# ጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

## የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

## የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በኦሮምኛ አፍ-ፈት እና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንትና በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

አንድነት አራጌ

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ የሁለተኛ ዲግሪ ክፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ነሐሴ፣ 2016 ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

ጅማ ዩኒቨርሲቲ

ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ

የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር

# በኦሮምኛ አፍ-ፈት እና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንትና በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

በ

አንድነት አራጌ

በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ የሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት

ዋና አማካሪ ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር)

ረዳት አማካሪ ለማ ንጋቱ (ዶ/ር)

ነሐሴ፣ 2016 ዓ.ም

ጅማ ኢትዮጵያ

**ጅማ ዩኒቨርሲቲ**

**ሶሻል ሳይንስና ሒዩማኒቲስ ኮሌጅ**

**የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሁፍ-አማርኛ ትምህርት ክፍል**

**የድህረ ምረቃ መርሃ ግብር**

# በኦሮምኛ አፍ-ፈት እና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንትና በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት (የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)

**በ**

**አንድነት አራጌ**

**በአማርኛ ቋንቋ ማስተማር ስነዘዴ የሁለተኛ ዲግሪ ከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት**

| የአማካሪ ስም | ቀን | ፊርማ |
|---|---|---|
| ______________ | ______________ | ______________ |

| የፈታኞች ስም | ቀን | ፊርማ |
|---|---|---|
| ______________ | ______________ | ______________ |
| ______________ | ______________ | ______________ |
| ______________ | ______________ | ______________ |

# ምስጋና

ለዚህ ጥናታዊ ፅሁፍ ለስራዬ መሳካት እርማቶችን አስተያየቶችን በመስጠት ለረዱኝ ዋና አማካሪዬ ጥበቡ ሽቴ (ዶ/ር) ረዳት አማካሪዬ ለማ ንጋቱ (ዶ/ር) የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። ለስራ ያላቸውን ፍቅርና ሰአት አክባሪነታቸውንም ሳላደንቀው አላልፍም። በመቀጠልም ጅማ ዩኒቨርስቲ ቤተ መጸሐፍት ሰራተኞች ለአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ክፍል መምህራን በሙሉ ምስጋናዬን አቀርባለሁ። እንዲሁም ሳይማር ላስተማረኝ እናቴ እነዲሁም ልምዱን በማካፈል በሃሳብና ቴክኒክ ብማማከር ለረዳኝ መምህር ብርሃኑ ደጀኔ በመጨረሻም እንድማር የት/ርት ሰዓት በማመቻቸት ከጎኔ በመሆን ያበረታቱኝን የት/ቤቱን ርዕሰ መምህር እና የትምህርት ባልደረቦቼን እጅግ በጣም አመሰግናለሁ።

# አጠቃሎ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ አማርኛ አፈ ፈትና ኢ-አፈ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንትና ጥናት ማድረግ ነው። አጥኚው መረጃውን ሰብስቦ ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በዋናነት ቅይጥ ምርምር ዘዴ እና በደጋፊነት አይነታዊ ምርምር ስራ ላይ አውሏል። በመሆኑም በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አስረኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች በድምሩ 348 ሲሆኑ ወንዶቹ 226 ሴቶቹ ደግሞ 122 ናቸው። ከነዚህም መካከል 15 ተማሪዎች አማርኛ አፍ ፈት ሲሆኑ 22 ተማሪዎች ደግሞ ኢ-አፍ ፈት ድምር 37 ተማሪዎች በቀላል የእጣ ናሙና ሲመረጡ ሶስቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራንን በጠቅላይ ናሙና ዘዴ ተመርጧል። የጥናቱ የመረጃ ምንጮች ከዚህ ርእስ ጋር የሚቀራረቡ ጉዳዮችን ለመሰብሰብ፤ የሰነድ ፍተሻ፣ የተጠኝዎች የጽህፈት ክሂል ፈተና እና በተጠኝዎች ከሚሞሉ ጽሁፍ መጠይቅ የሚገኙ የመረጃ ግብዓቶች ናቸው። ከጥናት ውጤቱ መረዳት እንደተቻለ አማርኛ ቋንቋ አፍ ፈት ተማሪዎች ከአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የተሻለ የቃላት አጠቃቀም ችሎታ እንዳላቸው፤ አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በቃላት አጠቃቀምና በአረፍተ-ነገር አወቃቀር በጣም ችግር እንዳለባቸው፤ በጠቅላላ ድምር ውጤት አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ከአፍ ፈት ተማሪዎች በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው የተሻሉ፤ አማርኛ ኢ-አፍ-ፈት ተማሪዎች ከኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በአንቀጽ አደረጃጀት ችሎታቸው የተሻሉ፤ በተማሪዎች የድርሰት ጽህፈት ፍላጎትና መምህራን ለጽህፈት ትምህርት በሚሰጡት ትኩረት ተማሪዎች ድርሰት ለመፃፍ ከፍተኛ የሆነ ተነሳሽነት እንዳላቸው፤ መምህራን ለክሂል ትኩረት ሰጥተው እንደማያስተምሩ እና ቢያስተምሩም ተማሪዎች ለሚጽፉት ድርሰት በራሳቸው ፍላጎት የሚመርጡት ርዕስ ሳይሆን በመምህራኑ እደሚመረጥላቸው እና ተማሪዎች ለፃፉት ድርሰት መምህራኑ ወዲያውኑ ምጋቤ ምላሽ እንደማይሰጧቸውና ስህተታቸውን አውቀው ለወደፊት የተሻሉ ሆነው ለመገኘት የሚያስችላቸው ሁኔታ እንደሌላቸው በጥናቱ ተረጋግጧል።

*መውጫ* **ገጽ**

ምስጋና ........ i
አጠቃሎ ........ ii
የሰንጠረዥ ዝርዝር ........ vi
ምዕራፍ አንድ መግቢያ ........ 1
1.1 የጥናቱ ዳራ ........ 1
1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ........ 2
1.3 መሰረታዊ የጥናቱ ጥያቄዎች ........ 3
1.4 የጥናቱ ዓላማ ........ 3
1.4.1 የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ ........ 3
1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ ........ 3
1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት ........ 3
1.6 የጥናቱ ወሰን ........ 4
ምዕራፍ ሁለት ........ 5
ክለሳ ድርሳናት ........ 5
2.1 ጽነሰ-ሀሳባዊ መሠረቶች ........ 5
2.1.1 የጽህፈት ክሂል ምንነት ........ 5
2.1.2 የጽህፈትን ክሂል ማስተማር የሚያስገኘው ጥቅም ........ 5
2.1.3 የጽህፈት ባህርይ ውስብስብ መሆን ........ 6
2.1.3.1 ስነልቦናዊ፣ ስነልሳናዊ እና አዕምሯዊ ባህሪያት ........ 7
2.1.4 የጽህፈት ክሂል ትምህርት አቀራረቦች ........ 8
2.1.4.1 ውጤት ተኮር አቀራረብ ........ 8
2.1.4.2 ሂደታዊ አቀራረብ ........ 8
2.1.5 የጽህፈት ክሂል መልመጃ አይነቶች ........ 9
2.1.6 ለመፃፍ የሚያነሳሱ ተግባራት ........ 9
2.1.6.1 ተግባራዊ የጽህፈት መልመጃዎች ........ 9
2.1.6.2 የስሜት መግለጫ ጽሁፎች ........ 10
2.1.6.3 ትምህርት ቤት ተኮር የጽህፈት መልማመጃዎች ........ 10
2.1.7 የጽህፈት ችሎታ መመዘኛ ነጥቦች ........ 11
2.1.7.1 የቃላት አመራረጥ ........ 11

2.1.7.2 የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ...... 11
2.1.7.3 የስርዓ-ተነጥብ አጠቃቀም ...... 11
2.1.7.4 የአንቀጽ አወቃቀር ...... 12
2.1.7.5 የአንቀጽ ቅንብር /ውህድት/ ...... 12
2.1.7.6 የአንቀጽ ተያያዥነት ...... 12
2.1.7.7 የአንቀጽ አንድነት ...... 12
2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ...... 13
ምዕራፍ ሦስት ...... 15
3. የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ ...... 15
3.1 የጥናቱ ንድፍ ...... 15
3.2 ጥናቱ አካላይ ...... 15
3.3 የናሙና አመራረጥ ...... 15
3.2.1 የትምህርት ቤት የናሙና አመራረጥ ...... 15
3.3.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ ...... 16
3.3.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ...... 16
3.4 የጥናቱ መረጃ ምንጮች ...... 16
3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ...... 16
3.5.1 የድርሰት መጻፍት እና ድርሰታቸውን መመርመር ...... 16
3.5.1.1 የድርሰት መጽሐፍ ርዕሶች መረጣ እና አስተራረም ...... 17
3.5.1.2 የጽህፈት ፈተናው አስተራረም ...... 18
3.5.1.3 የጽሑፍ መጠይቅ ...... 18
3.6 የመረጃ አተናተን ...... 18
3.6.1 የጽህፈት መረጃ አተናተን ...... 18
3.6.2 የጽሁፍ መጠይቅ አተናተን ...... 19
ምዕራፍ አራት ...... 21
4. የመረጃ ትንተና ...... 21
4.1. የቃላት አጠቃቀም ...... 21
4.2. የአረፍተ-ነገር ሰዋሰዋዊነት ...... 26
4.3. የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ...... 34
4.4. የአንቀጽ አደረጃጀት ...... 39
4.5. በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የታዩ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም ...... 42
4.6. ተማሪዎች ለጽሕፈት ችሎታ ያላቸው ፍላጎት ...... 46

4.7. መምህራን ለጽሕፈት ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት ....................................47
ምዕራፍ አምስት ....................................................................................................50
5. ማጠቃለያና አስተያየት ....................................................................................50
5.1 ማጠቃለያ ....................................................................................................50
5.2 አስተያየት ....................................................................................................51
ዋቢ ጽሁፎች ....................................................................................................53
አባሪ “ሀ” ....................................................................................................57
አባሪ “ለ” ....................................................................................................59
አባሪ “ሐ” ....................................................................................................62

## የሰንጠረዥ ዝርዝር

ሰንጠረዥ 1. ድርሰት እንዲጽፉ የተደረጉ ተማሪዎች ብዛት ........ 17
ሰንጠረዥ 2. የተጠኝ ተማሪዎች የቃላት አጠቃቀም ችሎታ ........ 21
ሰንጠረዥ 3. የተጠኝ ተማሪዎች የቃላት ምርጫ ........ 23
ሰንጠረዥ 4 የተጠኝዎች አረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታ ........
ሰንጠረዥ 5 ተጠኝዎች ድርሰት ሲጽፉ የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታ ........ 28
ሰንጠረዥ 6 የተጠኝዎች የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ........ 34
ሰንጠረዥ 7. ተጠኝ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ........ 35
ሰንጠረዥ 9. ተጠኝ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የአንቀጽ አደረጃጀት ........ 41
ሰንጠረዥ 10. የተጠኝ ተማሪዎች በፃፉት ድርሰት ውስጥ የታዩ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም ... 42
ሰንጠረዥ 11. የተጠኝ ተማሪዎች የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም ችሎታ ........ 44
ሰንጠረዥ 12. ተጠኝ ተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ያላቸው ፍላጎት ........ 46
ሰንጠረዥ 13. ተጠኝ ተማሪዎች መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ........ 47
ሰንጠረዥ 14. ተጠኝ ተማሪዎች የጽህፈት ትምህርት ስማር ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥልኝ መምህሩ ነው ........ 48

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

የቋንቋ ትምህርት መሰረታዊ ዓላማው የቋንቋ ክሂሎችን ማዳበር፣ የስነ ጹሁፍ እና የስነ ልሳን ዕውቀቶችን ማዳበር ነው። የጽህፈት ክሂል ከአራቱ የቋንቋ መሰረታዊ ክሂሎች አንዱ ነው። አፍ ፈትም ሆኑ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በመደበኛ ትምህርት ቤት ውስጥ ይለምዱታል። በሁለተኛ ቋንቋ ልምድ ሂደት ጽህፈትን ተጠቅሞ ሀሳብን ለመግለፅ የቋንቋውን ሰዋሰውና ማህበራዊ የቋንቋ አጠቃቀም ማወቅ ያስፈልጋል በማለት Ring born (1992) and Brown (1994) ያስረዳሉ። የማንኛውም ቋንቋ ትምህርት ዋና ዓላማው የተማሪዎችን የቋንቋ ክሂሎችን ማዳበር ነው። ይህንን ተግባር በተገቢው መንገድ ለመፈጸም ያስችል ዘንድ ለአራቱ የቋንቋ ክሂሎች ማለትም ማዳመጥ፣መናገር፣ ማንበብና መጻፍ ተገቢውን ትኩረት የሰጠ የትምህርት ይዘት አዘጋጅቶ ማቅረብ ያስፈልጋል። በዚህም የመማሪያ መጽሀፍ ውስጥ የሚቀርብ የክሂል ይዘት ለአንድ ክሂል የማያዳላ እና ሁሉንም በተገቢው መንገድ አጣጥሞ የያዘ መሆን ይኖርበታል በማለት Harmer (1991፡52) ይገልፃሉ።

ከላይ ምሁራኑ የገለጹት ሀሳብ የጽህፈት ክሂል ከባድና ረጅም ጊዜን የሚጠይቅ መሆኑን ለማመላከት ነው። በመሆኑም አጥኚው በምሁራኑ ሀሳብ ትክክለኛና ጥናቱንም የሚደግፍ ሆኖ አግኝቶታል። እንዲሁም በተመሳሳይ መልኩ Richards እና Renandya (2002, 303) "ለሁለተኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ቋንቋውን በሚገባ ተጠቅመው፣ ሀሳብ አሰባስበውና አዳብረው ለመፃፍ የማያጠራጥር ሀቅ ነው" በማለት ሀሳባቸውን ያጠናክሩታል። በሌላ በኩል Abiy (2013, 58) "ጽህፈትን በሁለተኛ ቋንቋ ለማዳበር የአፍ መፍቻ ቋንቋ የጽህፈት ክሂል ትልቅ አስተዋጽኦ አለው" በማለት ያብራራሉ። ይህም ማለት ተማሪዎች በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው የጽህፈት ክሂልን ትኩረት ሰጥቶ ማስተማር በቀጣይ በሁለተኛ ቋንቋና በውጭ ቋንቋ ለሚማሩት የጽህፈት ትምህርት መንገድን ቀላል እንደሚያደርግላቸው ለማሳየት ነው።

በመሆኑም ጥሩ የመጻፍ ክሂል፣ ለስነ ትምህርታዊ ብቃትና ለተሳካ ውጤት፣ ለተለያዩ ስራዎች እና ሙያዎች እጅግ በጣም አስፈላጊና ጠቃሚ ነው። ይህ አስፈላጊና ጠቃሚ ክሂል በአማርኛ ቋንቋ ረገድ በአሁኑ ጊዜ ምን ይመስላል? በአጠቃላይ፣ ዛሬ በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ክሂልን አስመልክቶ የተማሪዎችም ሆነ ሙያቸው አስገድዷቸው የሚጽፉ ፀሀፍት ጽሐፎች ደካማ እንደሆኑ ሌሎች ጥናቶችም አመላክተዋል። ከነዚህም ጥናቶች

መካከል ሰይድ (1993)፣ አለማየሁ (1998)፣ ጌታቸው (2001) እና ኢሳያስ (2002) ተጠቃሽ ናቸው። አጥኚዎቹ በጥናታቸው እንዲሰፍሩት በአንደኛ ደረጃም ሆነ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ ተማሪዎች የጽህፈት ችሎታቸው በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ አብራርተዋል።

ይሁን እንጂ የዚህ ችግር ምክንያት የቋንቋ ትምህርት በሀገራችን የትምህርት መርሃ-ግብር ወይም በስርዓተ-ትምህርት ካለመካተት የመነጨ አይደለም። ችግሩ፣ ቋንቋው በትምህርትነት ቢቀርብም የተዳከመና በተለይ ከአንደኛ ደረጃ እስከ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ደረስ ትኩረት የተነፈገው እንደሆነ ካረጋገጠ በኋላ አማርኛ አፍ ፈት እና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችን መገምገም፤ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መፈተሽ፤ በአጠቃላይ በጽህፈት ክሂል ላይ ያላቸውን ፍላጎት እና ችሎታ በማጥናት ጉድለቱን ማሳየት ይሆናል። ስለዚህ ይህም ጥናት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች በክሂል ምን ደረጃ ላይ እንዳለ አማርኛ አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ለማጥናት ሲነሳ ቀደም ብሎ በቀረቡት አጥኝዎች ያገኙት ውጤት ምንድን ነው? ለሚለው ጥያቄ መልስ ይሰጣል ብሎ በማሰብ ነው።

## 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አጥኝው ጥናቱን ለማካሄድ ያነሳሳው ምክንያት በአሁኑ ጊዜ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ መፃፍ እማይችሉበት ደረጃ ላይ መድረሳቸውን ካለፈው ልምድ በተግባር ያየው ነው። በመሆኑም በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አስረኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎችን የጥናቱ ተሳታፊ ለማድረግ በአጥኚው ተመርጧል። ይህም ትምህርት ቤት የተመረጠበት ምክንያት አጥኚው የሚሰራበት ቦታ በመሆኑና የተማሪዎችን ችሎታ ጠንቅቆ ስለሚያውቅ ነው። በተጨማሪም ቀደም ሲል የተገለጹት አጥኚዎች ከደረሱበት ድምዳሜና ምሁራኑ ከሰጡት አስተያየት በመነሳት በአዲሱ ትምህርት ፖሊሲ አማርኛ ቋንቋን እንደ አፍ መፍቻና እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ተምረው ወደ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ከገቡ ተማሪዎች ውስጥ የጽሕፈት ክሂል ችግሮች በየትኞቹ ተማሪዎች ላይ እነደሚስተዋሉና በጽህፈት ችሎታቸው የትኞቹ እነደሚሻሉ የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ፍላጎት ስላደረበት ይህን ጥናት ለማጥናት ተነሳስቷል።

## 1.3 መሰረታዊ የጥናቱ ጥያቄዎች

1. አማርኛ አፍ ፈት እና ኢ-አፍ ፈት የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ምን ዓይነት ስህተቶችን ይፈጽማሉ?
2. አማርኛ አፍ-ፈት እና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?
3. አጠቃላይ በጽህፈት ክሂል ላይ ያላቸውን ፍላጎት እና ችሎታ ምን ደረጃ ላይ ይገኛል?

## 1.4 የጥናቱ ዓላማ

### 1.4.1 የጥናቱ ዓቢይ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዓቢይ ዓላማ በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚማሩ አማርኛ አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና ጥናት ማድረግ ነው።

### 1.4.2 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማ

- ❖ አማርኛ አፍ ፈት እና ኢ-አፍ ፈት የአማርኛ ትምህርት ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችን መገምገም፤
- ❖ አማርኛ አፍ-ፈት እና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መፈተሽ፤
- ❖ አጠቃላይ በጽህፈት ክሂል ላይ ያላቸውን ፍላጎት እና ችሎታ ማጥናት ናቸው።

## 1.5 የጥናቱ አስፈላጊነት

ይህ ጥናት ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸውን ስህተቶች ለመለየት ሲሆን የሚከተሉት ጠቀሜታዎች ይኖሩታል ተብሎ ይታሰባል።

1. በአማርኛ ቋንቋ ለሚያስተምሩ መምህራን የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው አማርኛ ያልሆኑ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶችና የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ በመገምገምና የስህተት ምንጭ በመለየት ልዩ እገዛ እንዲደርግላቸው ፍንጭ ይሰጣል።

2. ት/ቤቱ በአማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍ ፈት የሆኑ ተማሪዎች ድርሰት በአማርኛ ቋንቋ ሲጽፉ ስህተታቸውንና የስህተታቸውን ምንጮችን ምን እንደሆነ በመገንዘብ ለመምህራኖቹ ልዩ ስልጠና ለመስጠት ያስችላል።
3. በዚህ መስክ ወደ ፊት ጥናት ለሚያጠኑ አጥኚዎች የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል።

## 1.6 የጥናቱ ወሰን

ጥናቱ የሚካሄደው ኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ጅማ ዞን በማና ወረዳ በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች በ2016 ዓ.ም ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ የሚገኙ በኦሮምኛ ቋንቋ አፍ-ፈት የሆኑ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ በሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና ላይ ያተኮረ ነው።

# ምዕራፍ ሁለት
# ክለሳ ድርሳናት

## 2.1 ጽንሰ-ሀሳባዊ መሠረቶች

### 2.1.1 የጽህፈት ክሂል ምንነት

ጽህፈት በትዕምርቶች አማካኝነት ሀሳብን በወረቀት ላይ ማስፈር መሆኑን የተለያዩ ምሁራን በጥናታቸው አብራርተዋል። ከነዚህም መካከል Byrne (1991,1) "ጽህፈት የንግግር ደምፆችን የሚወክል ትዕምርቶችን ተጠቅሞ ሀሳብን በወረቀት ላይ የምናሰፍርበት ሂደት ነው" ብለዋል። ይህን ሀሳብ በማጠናከር Harmer (1991) እና Zamel (1985) ንግግር ድምፅ ከማመንጨት በላይ እንደሆነ ሁሉ ጽህፈትም ትዕምርቶችን አቀናብሮ የሚያቀርብ ነው በማለት በጥናታቸው አብራርተዋል።

ከላይ ምሁራኑ ለማብራራት የፈለጉት የአንድ ቋንቋ ድምፆች ከሚወክሏቸው ምልክቶች ጋር እየተዛመደ በወረቀት ላይ በማስፈር መልዕክት የሚተላልፍበት ክሂል መሆኑን ነው። ጽህፈት አንደ የመግባቢያ መሳሪያ እንደመሆኑ መጠን መልዕክት ተቀባዩና መልዕክት ላኪው በወረቀትና በብዕር አማካኝነት መልዕክት ይለዋወጣሉ። እንዲሁም በድምጽ ምልክቶች አማካኝነት ሀሳብን በወረቀት ላይ በማስፈር ከሌላ አካል ጋር ለመግባባት ያስችላል። በተጨማሪም ከንግግር ጋር የቀረበ ግንኙነት አለው።

በአጠቃላይ የጽህፈት ክሂል አካልና አዕምሮን በማስተባበር ድምፆችን በምልክቶች በመወከል ሀሳብን ለአንባቢ የምናቀርብበት ክሂል ነው። በጽሐፍ የሚቀርበው ሀሳብ ሊያግባባ የሚችለው የቋንቋውን ስርዓት የጠበቀ ከሆነ ብቻ ነው። በዚህ መንገድ ሀሳብን ማስተላለፍ እንዲቻል ሰፊ ልምምድ ማድረግ ያስፈልጋል። ጽሐፍ ከተግባር ጋር ጥብቅ ግንኙነት ያለው በመሆኑ በተደጋጋሚ በሚደረጉ ሙከራዎች ያድጋል፣ ይዳብራል፣ ይበለጽጋል፣ እንዲሁም ጥሩ ፀሀፍት እንዲፈጠሩ ያደርጋል።

### 2.1.2 የጽህፈትን ክሂል ማስተማር የሚያስገኘው ጥቅም

የጽህፈት ትምህርት ከንባብ ትምህርት ጋር በጣም የተቆራኘ ግንኙነት አለው። ከነዚህ ሁለት ክሂሎች ቀዳሚ ተግባር ፊደል ከማስለየት ይጀምራል። የምናነበው በፊደል የተገነባ ነገር ነው። ስለዚህ የጽህፈት ትምህርት የሚያስገኘው ጥቅም በቋንቋው ውስጥ ያለ ድምፆች የሚወክሏቸውን ምልክቶች ማስለየት ነው። ምንም እንኳ ፊደልን የማስለየት ተግባር የመጀመሪያው የጽህፈት ትምህርት አላማ ቢሆንም እንደ ተማሪዎቹ

እድሜ፣ የትምህርት ደረጃና ፍላጎት መሠረት በተለያዩ ደረጃዎች የጽህፈት ትምህርት አላማ ሊለያይ ይችላል።

የጽህፈት ትምህርት የተለያዩ የመማር ፍላጎትን ለማስገኘት እንደሚረዳ፤ የተለያዩ ክሂሎች በማቀናጀት መማር እንደሚያስችልና በመደበኛና መደበኛ ያልሆኑ ፈተናዎችን ለማቅረብ እንደሚያገለግል ተብራርተዋል። እንዲሁም የጽህፈት ትምህርት በአንድ ቋንቋ ውስጥ ያሉ ድምፆችን የሚወክል የተለያዩ ምልክቶችን ከማሳየት አንስቶ ሀሳብን ተጠየቃዊና ቅደም ተከተላዊ በሆነ መንገድ ለማስተላልፍ የሚያስችል ብቃትን ያጎናጽፋል። በአጠቃላይ ከላይ የቀረቡት የጽህፈት ትምህርት የማስተማር ጥቅሞችን መሠረት በማድረግ ተጠኚ ተማሪዎች እምን ደረጃ ላይ እንደሚገኙ ለመመርመር ይጠቅማል።

### 2.1.3 የጽህፈት ባህርይ ውስብስብ መሆን

የጽህፈት ክሂል በቀላል የሚጨበጥ ክሂል አይደለም፡፡ ክሂል ውስብስብና ረቂቅ የሆነ ክሂል ነው፡፡ በተለይ ደግሞ አስቸጋሪነቱን የሚያጎላው እንደማዳመጥና መናገር በልምድ ሳይሆን በትምህርት ብቻ የሚገኝ መሆኑ ነው። የጽህፈት ስራ ሀሳብን ከማደራጀት ጋር በጣም የተቆራኘ ነው፡፡ አዕምሯዊ እና አካላዊ ስራ የሚጠይቅ ነው፡፡ ሀሳብን በጽሑፍ ለማስፈር ጊዜ ይወስዳል።

እነዚህ ሁሉ ባህሪያቱ ውስብስብነቱንና አስቸጋሪቱን ያሳያሉ። ብዙ ጊዜ ወስዶ ተጽፎም በመጨረሻ ውጤቱ የታሰበውን ያህል የተፈለገውን መልዕክት ሊያስተላልፍና ሊያረካ ይችላል። የጽህፈት ክሂል ምልክቶችን በወረቀት ላይ ከማስፈር ያለፈ ነገር ነው፡፡ አንደ የተዋጣለት ጽሁፍ አጠናቅሮ ለማቅረብ ብዙ ነገሮችን ማወቅ ይጠይቃል። ከነዚህ ችሎታዎች መካከል የሚከተሉት ይጠቀሳሉ።

1 ሀሳብና መረጃዎችን አቀናጅቶ አጠናቅሮ ማቅረብ፣

2. ከአሻሚነት ነፃና ግልጽ በሆነ መንገድ ማቅረብ፣

3. ለአጽንኦት ሲባል ውስብስብ ያለ ሰዋስዋዊ ሰርዓቶችን አለመጠቀም፣

4. ጥንቃቄ የተሞላ የቃላት ምርጫና አጠቃቀምን መከተል፣

5. ተገቢውን የሰዋስው አጠቃቀም መከተልና የአረፍተነገር መጠን መወሰንን ማወቅ።

ከላይ የቀረቡት የጽህፈትን ውስብስብነት የሚያሳዩት ነጥቦችና ጽህፈትን አጠናቅሮ ለማቅረብ የሚረዱት ነጥቦች ተጠኝ ተማሪዎች በፃፉት ድርሰት ከተነሱት አምስት ነጥቦች የትኛው ላይ የተሻለ ትኩረት እንዳላቸው ለማወቅ አስችሏል።

### 2.1.3.1 ስነልቦናዊ፣ ስነልሳናዊ እና አዕምሯዊ ባህሪያት

በጽህፈት ትምህርት ላይ ተጽእኖ ከሚያሳድሩት መካከል ስነልቦናዊ፣ ስነልሳናዊና ስነአዕምሯዊ ሁኔታዎች እንደሆኑ Byrne (1991), Richards (1990) እና Norrish (1990) ያስረዳሉ። በመሆኑም ቀጥሎ የተወሰኑትን በዝርዝር እንመለከታለን።

**ሀ. ስነልቦናዊ ባህሪ፡-** ጽህፈት የማፍለቅ ተግባር የሚከናወንበት ክሂል እንደመሆኑ መጠን አንባቢን እያሰቡ መፃፍ የማይቀር ነው። ፀሀፊውም መልዕክቱን ለአንባቢ ግልጽና ሳቢ በሆነ መንገድ ለማድረስ ሲል ከወዲሁ በሀሳብና በጭንቀት የሚሞላበት ሁኔታ ይኖራል፡፡ ይህም የጽህፈት ክሂልን አስቸጋሪ ያደርገዋል።

**ለ. ስነልሳናዊ ባህሪ፡-** በጽህፈት አማካኝነት ሀሳብን በሚገባ ለማስተላለፍ ተዘጋጅቶ የሚቀርበውን መልዕክት ለመረዳት የቋንቋውን ውስጣዊ ባህሪ ማወቅ ወሳኝ ነው። በንግግር ሂደት ውስጥ ጠቃሚነት የሌላቸውንና የምንተዋቸውን ሁሉ ደግመን በማለት ወይም እንደገና አስተካክለን ለመናገር እድል ስላለን ልናስተካክለው እንችላለን። ይህ ሁኔታ በጽህፈት ጊዜ የተለየ ነው። ምክንያቱም ስንጽፍ በጣም ተጠንቅቀን፣ አስበንና ጊዜ ወስደን እያንዳንዱን ቅንጣት አስተካክለን ማቅረብ ይኖርብናል በማለት Byrne (1991) እና Norrish (1990) ያስረዳል።

**ሐ. ስነአዕምሯዊ ባህሪ፡-** ጽህፈት በልምድ ሳይሆን በትምህርት ሂደት የሚገኝና የአዕምሮን ውስጣዊ ረቂቅ ተግባር የሚጠይቅ ውስብስብ ክሂል ነው፡፡ እንዲሁም እንደየደረጃችን ፈተናን ለማለፍ አሊያም ለክሂልነት ብቻ የምንማረው ጥበብ አይደለም።

ይልቁንም ትምህርቱ ሌሎች ክሂሎችን ለመማርና ተጨማሪ እውቀቶች ለመቅሰሚያነት ያገለግላል፡፡ የጽህፈት ክሂል እጅን፣ ዓይንና አዕምሮን በማጣመር ተግባቦትን ለማፍጠንና ገጠመኞችን ለማካፈል የሚያገለግል ስለሆነ ውስብስብ የሆነ አዕምሮታዊ ባህሪ አለው፡፡ ክሂልንም ለማዳበር ሰፊ ጊዜና በቂ ልምምድ የሚጠይቅ ጊዜ ወሳጅ ክሂል ነው።

### 2.1.4 የጽህፈት ክሂል ትምህርት አቀራረቦች

በአሁኑ ጊዜ እየተሰራባቸው ያሉት የጽህፈት ክሂል አቀራረብን ውጤት ተኮር አቀራረብ እና ሂደታዊ አቀራረብ ናቸው በማለት Nunan (1989) እና Richards (1990) በሁለት እንደሚመደቡ ያስረዳል።

#### 2.1.4.1 ውጤት ተኮር አቀራረብ

ውጤት ተኮር አቀራረብ አጠቃላይ ትኩረቱ ከጽህፈት ሂደት ይልቅ ተማሪዎች በሚያፈልቁት የመጨረሻ ውጤት ላይ ነው። በዚህ አመለካከት የተማሪዎች የመፃፍ ብቃት ከፍ ሲል ውስብስብ የጽህፈት ተግባራትን የመቆጣጠር ችሎታን ያዳብራሉ፡፡ ይህ ከሆነ ደግሞ ብዙ የተለያዩ ስልቶችን ይጠቀማሉ። የአረፍተ-ነገርና የአንቀጽ አደረጃጀት ቅንብር ይካናሉ በማለት Nunan (1989) እና Richards (1990) ይገልፃሉ፡፡ ይህ አቀራረብ የጽህፈትን ምንነት የሚለካው የሰዋስው ህግጋትን ተክተሎ በጽህፈት ከመተግበር አንፃር ሲሆን አይነተኛ ትኩረቱም በስተመጨረሻ ተጠናቆ የሚቀርበው ሥራ ላይ እንጂ ጽሑፍ እንዴት እንደሚዘጋጅ በሚፈፀመው ሂደት ላይ አይደለም፡፡ አቀራረቡ በአንድ በኩል ተማሪዎች ልዩ ልዩ የጽህፈት ሥራዎችን እንዲያዘጋጁ የሚረዳ ሲሆን በሌላ በኩል ስህተት እንዳይሰሩ የሚከለክል እንደሆነ Richards (1990) ያስረዳሉ። ለቅርጽ ከፍተኛውን ትኩረት የሚሰጠው በዚህ አቀራረብ ብዙውን ጊዜ በድርሰት ርዕስ መምህሩ ተጽእኖ የሚያደርግ ሲሆን አረፍተ-ነገር ምስረታ፣ ባድ ቦታ መሙላት፣ አረፍተ-ነገር ማስፋፋት፣ አንቀጽ ማዳበርና ወዘተ. የተለመዱ ተግባሮች ናቸው በማለት Pincas (1982), Kamrul እና Mohd. (2010) ያስረዳሉ።

#### 2.1.4.2 ሂደታዊ አቀራረብ

ተመራማሪዎች ውጤት ተኮር አቅራረብ ጽህፈትን በማስተማር ረገድ ድክመት እንዳለው በቅርብ አመታት አመልክተዋል። ውጤት ተኮር አቀራረብ አትኩሮቱ ክሂልን ከማሳደግ ይልቅ ውጤት ላይ መድረስ ላይ ነው። ተማሪው በሂደት የተለያዩ ደረጃዎችን እያለፈ እንዲመጣ ሳይሆን የታሰበው ግብ ላይ እንዲደርስ የሚያደርግ አቀራረብ ነው፡፡ በመሆኑም የጥሩ ፀሀፊዎች ሂደታዊ አቀራረብ ምርጫቸው አድርገዋል። ሂደታዊ አቀራረብ አይነተኛ መገለጫው ፀሀፊው በመፃፍ ሂደት የሚፈጽማቸውን ተግባራት በመግለጽ ላይ ማተኮር ነው። በዚህ አቀራረብን በትክክለኝነቱ ምትክ የፀሀፊው የአፃፃፍ ሂደት ከፍተኛ ግምት ይሰጠዋል። የዚህ ፈለግ አራማጆች ትኩረት የሚያደርጉት በመጨረሻ ተጠናቆ በሚቀርበው የጽህፈት ውጤት ላይ ሳይሆን ወደ እዚያ ለመድረስ የሚያስችለው ሂደት ላይ ነው። ፀሀፊውም አዘውትሮ እራሱን የሚጠይቀው ስለጽሁፉ አላማና ስለአንባቢያን ሳይሆን ጽሁፍን እንዴት ልጀምረው እንዴትስ ሀሳቤን አቀናጅቼ

ልፃፊው የሚል ጉዳይ ላይ ነው በማለት Raimes (1983) ያስረዳሉ። በዚህ የጽህፈት አቀራረብ ተማሪዎች ድርሰታቸውን የሚጽፉት በውጤታዊ አቀራረብ እንደሚዘወተረው በመምህሩ ተወስኖ በሚሰጣቸው ርዕስ አይደለም። እራሳቸው የሚሰማቸውን ርዕስ ይመርጣሉ። የጽሁፋቸውን ረቂቅ ለመምህራን ለጓደኞቻቸው ያሳያሉ። የሚያገኙትም ምላሽ ይበልጥ እንዲያስቡበት ይገፋፋቸዋል። በጽህፈት ሂደት ውስጥ የተለያዩ ደረጃዎች አሉ፡፡ የጽህፈት ስራ የሚያከናውነው ሰው ሊያከናውናቸው የሚገቡ ነገሮች ለመፃፍ መነሳት ሀሳቦችን ማገናኘት፣ ሀሳብን በቢጋር መልክ ማዘጋጀት፣ ማስታወሻ መውሰድና የመጀመሪያውን ረቂቅ መፃፍ፣ መከለስ፣ እንደገና ማቀድ፣ ደግሞ ማርቀቅ በመጨረሻም ለህትመት ማዘጋጀት በተባሉት ክዋኔዎች ውስጥ እንደሚያልፉ Richards (1990) እና Hedge (1988) ያብራራሉ።

### 2.1.5 የጽህፈት ክሂል መልመጃ አይነቶች

ጽህፈትን በማስተማር ሂደት የጽህፈት ክሂል መልመጃ ተማሪዎችን የሚያግባቡ ወይም መልዕክት ያለው ጽሑፍ እንዲያዘጋጁ የሚያበረታቱ ቢሆኑ ይመረጣል። የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ተማሪው ክሂልን በመጠቀም መልዕክት ማስተላልፍና መግባባት እንዲችል በተግባር ሊተረጎሙ የማይችሉና በደረጃው ተማሪው በማህበረሰቡ ውስጥ ሊጠቀምባቸው የሚችሉ ሀሳቦችን ያልያዙ ሆነ ብለው የተዘጋጁ መልመጃዎች መሆን የለባቸውም። የጽህፈት ክሂል መልመጃዎች ሰዋስውና ቃላት ከማስተማር በላይ ተማሪው እንዴት መፃፍና ምን አይነት የአፃፃፍ ዘዴዎችን መከተል እንዳለበት የሚያስረዳ መሆን አለበት በማለት Pincas (1982) እና Raimes (1983) ያስረዳሉ።

### 2.1.6 ለመፃፍ የሚያነሳሱ ተግባራት

ተማሪዎች የጽህፈት ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ለማገዝ የተለያዩ መልመጃዎች ተሰጥቶ ተከታታይ ልምምድ እንዲተገብሩ ማድረግ ጠቀሜታው የጎላ ነው። በዚህ ልምምድ ሂደትም ተማሪዎች አዳዲስ ልምዳችን ያዳብራሉ፡፡ የጽህፈት ችሎታቸውንም ቀስ በቀስ ወደ ላቀ ደረጃ ያሸጋግራሉ። ተማሪዎች እንደ ክፍል ደረጃቸው የጽህፈት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ የሚረዳ ሦስት የጽህፈት መለማመጃ ተግባራት እንዳለ Celce-*Murcia* (2001) ያስረዱለ። ተግባራቱንም ቀጥለን በዝርዝር እንመልከት።

#### 2.1.6.1 ተግባራዊ የጽህፈት መልመጃዎች

ተግባራዊ የጽህፈት መለማመጃዎች ቅደም ተከተላዊ ይዘት ያላቸው ናቸው። በዚህ ልምምድና ሂደትም በማለማመጃነት ሊያገለግሉ የሚችሉት አጭር መልዕክቶች፣ ቀላል ትዕዛዞች የክፍል ስራዎች ሲሆኑ እድገት እያገኙ ሲሄዱ የማስታወሻ፣ የግብዣ፣ የመልዕክት፣ የሰላምታና የምስጋና ጽሑፎችን እንዲጽፉ ያደርጋል። እነዚህንና

የመሳሰለትን የመልመጃ ስሌቶች በመጠቀም ተማሪዎች የተለየዩ ጽሑፎችን በክፍል ውስጥ ወይም ከክፍል ውጭ እንዲጽፉ በማድረግ የተማሪዎችን ፍላጎት ማነሳሳት ይቻላል በማለት Celce-*Murcia* (2001) ያብራራሉ።

### 2.1.6.2 የስሜት መግለጫ ጽሁፎች

ስሜት መግለጫ ጽሐፎች በማለት ከተጠቀሱት ውስጥ ለጓደኛ ደብዳቤ መፃፍ፣ ውልመመዝገብን፣ ስለሌች ያለንን አመለካከት ወዘተ. መፃፍን ያካትታል። ይሁን እንጂ ይህ አይነቱ ጽሁፍ የተማሪዎችን ውስጣዊ ፍላጎት የሚስቡ በመሆናቸው በከፍተኛ የክፍል ደረጃዎች ለሚገኙ ተማሪዎች እንጂ በዝቅተኛ ደረጃዎች ላይ ለሚገኙ ተማሪዎች እንደማይሆን Celce-*Murcia* (2001) ይጠቁማሉ።

### 2.1.6.3 ትምህርት ቤት ተኮር የጽህፈት መልማመጃዎች

ጽህፈትን ሕይወታዊ እንዲሆን የሚያደርገው ተማሪዎች በትምህርት ቤታቸው ላይ ተመስርተው ሲጽፉ ነው። ትምህርት ቤታቸው በተማሪዎች አቅራቢያ ስለሚገኝ በትምህርት ቤት ያለውን አጠቃላይ ሁኔታ ለመገንዘብ ቅርበቱ አስተዋጽኦ ስላለው የሚሰማቸውና የሚሰጣቸውን ሀሳብ ለማደራጀት ሁኔታው ምቹ ይሆንላቸዋል በማለት ትምህርት ቤት ተኮር ጽሑፎች የተማሪዎችን የጽህፈት ክሂል ለማለማመድ ያለውን ፋይዳ Celce-*Murcia* (2001) ያስገነዝባሉ።

ከላይ የተዘረዘሩትን ለጽህፈት የሚያነሳሱ ተግባራት Raimes (1983) እና Ur (1996) በሚከተለው መልኩ በዝርዝር አቅርበዋል፡፡ ተማሪዎችን እንዲጽፉ የሚያነሳሳቸው ጉዳዮች ተማሪዎች መጽሀፍ እንዲያነቡና ስላነበቡት መጽሀፍ እንዲጽፉ ማድረግ አንድ ጽሁፍ ካነበቡ በኋላ ያነበቡትን በራሳቸው አባባል ጨምቀው አሳጥረው እንዲጽፉ ማድረግ አንድ ስእል በማሳየት ከስዕሉ የተገነዘቡትንና የተሰማቸውን እንዲጽፉ ማድረግ ግላዊ የሕይወት ተሞክሯቸውን በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍለ ውጭ እንዲጽፉ ማድረግ ስለጓደኞቻቸው ወይም ስለሚያውቋት ሌላ ሰው እንዲጽፉ ማድረግ የተለያዩ ደብዳቤዎችን እንዲጽፉ ማድረግ፣ ለምሳሌ፣ የሰላምታ ደብዲቤ፣ የግል ደብዲቤ፣ ልዩ ልዩ የጥሪ ደብዲቤዎች ወይም የመስሪያ ቤት ደብዳቤዎች እንዲጽፉ ማድረግ ተማሪዎች በሬዲዮና ቴሌቪዥን ያዳመጡትን ዜና በራሳቸው የዜና ዘገባ እንዲያዘጋጁ ማድረግ ትምህርት ቤታቸውን በተመለከተ ጽሁፍ እንዲያዘጋጁ ማድረግ የመስክ ጉብኝት እንዲያደርጉ በመጋበዝ ስለተመለከቱትና ስለተገነዘቡት ነገር እንዲጽፉ ማድረግ የ የዘረዘሩ ሲሆን ትልቅ ትኩረት ሊደረግበት የሚገባ ነገር ፍላጎት ለጽህፈት ወሳኝ ጉዳይ መሆኑንም ያስገነዝባሉ።

### 2.1.7 የጽህፈት ችሎታ መመዘኛ ነጥቦች

አንድ ጽሐፍ የተዋጣለት ነው የሚባለው ከፊደል ቅርጽ አጣጣል አንስቶ የቃላት መረጣ፣ የሰዋስው አጠቃቀም፣ ተገቢ ስርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና የአንቀጽ አወቃቀር ያሉትን ችሎታዎች በአግባቡ ሲያካትት ነው። የጽህፈት ክሂለ የሰዋስው አገባብን ጠብቆ ቃላትን በአረፍተ-ነገሮች አቀናጅቶ የማቅረብ ችሎታ መኖር ብቻ ሳይሆን ሀሳብን በተገቢ መንገድ በማፍለቅ ተጠዪቃዊ በሆነ መንገድ የማደራጀትንም ችሎታ ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም Pincas (1982, 32) "የማግባባት ብቃቱ፣ ተጠይቃዊ አደረጃጀት፣ በቅርጽና በአቀራረቡ፣ በሰዋስው ቅንብር ደረጃውና በእጅ ጽህፈት፣ በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም መስፈርቶች የጽህፈት ክሂል ሊመዘንና ሊገመገም ይችላል" በማለት ሀሳቡን ያጠናክሩታል።

#### 2.1.7.1 የቃላት አመራረጥ

ሀሳብን በጽሐፍ አቀናብሮ ለማቅረብ የምንጠቀማቸው ቃላት ወሳኝ ናቸው፡፡ ጽህፈት ወዲያውኑ ግብረ-መልስ የሚገኝበት ስላልሆነ የሚመረጡት ቃላት ምስሌ ከሳች፣ ሳቢ፣ ለአውድ ተስማሚና ለዛ ያላቸው ሊሆኑ ይገባል። በመሆኑም አማረ (1986፣ 4) “ቃላት የደራሲ ቀኝ እጅ ናቸው። ደራሲ ያለ ቃላት ሌላ መሳሪያ የለውም፡፡ ጥረቱ ሊሳካም ሊከሽፍም የሚችለው ቃላትን በጥበብና በጥንቃቄ በመጠቀም ለቋንቋው ውበት ለማስገኘት ሲችል ነው” በማለት የቃላትን ጠቀሜታ አጽንኦት ሰጥተው አብራርተዋል። ይህም አባባል የሚያስገነዝበን አንድ ፀሀፊ ሀሳቡን በተገቢ መንገድ ለማስተላለፍ ከፈለገ ሲጽፍ፤ የሚመርጣቸው ቃላት ላይ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት።

#### 2.1.7.2 የአረፍተ-ነገር አወቃቀር

አንድ ፀሀፊ ሀሳቡን በጽሁፍ አማካኝነት ለማስተላለፍ ከፈለገ የቋንቋውን ትክክለኛ ስርዓት ተከትሎ መፃፍ አለበት። ሰዋስው እያንዳንዱን ቃላት እርስ በርሱ በማቀናጀት አረፍተ- ነገሮች የሚመሰረቱበት መንገድ ነው። ይህም ማለት ሰዋስው ሲባል ሀተታዊ፣ አፍራሽ ወይም ብዙ ቁጥር ወይም ጥያቄያዊ አረፍተ-ነገሮች ስንመሰርት የምንከተለው የቃላት አሰላለፍ ሁኔታ የሰዋስው ጉዳይ ነው በማለት Harmer (1994) ገልፀዋል።

#### 2.1.7.3 የስርዓ-ተነጥብ አጠቃቀም

ስርዓተ-ነጥቦች አንድ ጽሁፍ የተፈለገውን መልዕክት በተገቢ ሁኔታ መግለጽ እንዲችል የሚደረጉ ምልክቶች ናቸው። ስርዓተ ነጥቦች በጽሐፍ ውስጥ የሚዘረዘሩ ነገሮችን ለመለየት፣ ሀሳብን የሚያስተላለፈ አረፍተ-ነገሮች ማለቃቸውን ለማመልከት የፀሀፊውን ስሜት ለመግለጽና ወዘተ. ሊያገለግል ይችላሉ።

### 2.1.7.4 የአንቀጽ አወቃቀር

አንድ አንቀጽ ሀሳብን ለመግለፅ፣ ለማስረዳትና ለማብራራት በሚያስችሉ ዝርዝር አረፍተ- ነገሮችና በአንድ ዋና አረፍተ-ነገር (ኃይለቃል) የሚገነባ የሀሳቦች ጥንቅር ነው። አንቀጹ አንድ ዋና ሀሳብ ብቻ ሊያንፀባርቅ የሚችለው በኃይለ ቃለና በዝርዝር አረፍተ-ነገሮቹ መካከል የሀሳብ አንድነት ሲኖር ነው። በመሆኑም Pincas (1982, 55) "በአንቀጹ ውስጥ የሚገኙ ዝርዝር አረፍተ-ነገሮች በተገቢው መንገድ እየተያያዙ አንደን ሀሳብ ሊገልጹ የሚችሉ ሊሆን ይገባል" በማለት ሀሳቡን ያጠናክራሉ።

### 2.1.7.5 የአንቀጽ ቅንብር /ውህድት/

የአንቀጽ ቅንብር ሲባል በጽሁፍ ለማስተላለፍ የተፈለገውን ሀሳብ ለማብራራትና ለማስረዳት የሚያስችሉ ነገሮችን ባህሪ በመረዳት እንደ ክብደትና ቅለታቸው ከአጠቃላይ ወደ ዝርዝር ወይም ከዝርዝር ወደ አጠቃላይ በቅደም ተከተል የሚቀርቡበት ስሌት ነው። በአንቀጹ ውስጥ ያለውን መንደርደሪያ አረፍተ-ነገር መነሻ አድርጎ ሌሎች መንደርደሪያ አረፍተ-ነገሮችን የሚገልጹና የሚያከራክሩ ዝርዝር አረፍተ-ነገሮች በቅደም ተከተል ከክብደታቸውና ቅለታቸው አንፃር ከአቢይ ወደ ንዑስ ወይም ከንዑስ ወደ አቢይ እንደሚቀርቡ Raimes (1983) ያስረዳሉ።

### 2.1.7.6 የአንቀጽ ተያያዥነት

አንድን አንቀጽ የሚመሰርቱት አረፍተ-ነገሮች እርስበርሳቸው የተያያዙ መሆናቸውን ያመለክታል። አንቀጽን ሊመሰርቱ የሚችሉ ዝርዝር አረፍተ-ነገሮች እርስበርሳቸው በተገቢው ተያያገሮች ተቀናጅተው ለአንባቢ በቀላል ሊተላልፍ የሚፈለገውን መልዕክት ሊረዳ ይገባዋል። ከዚህም ሌላ በአንቀጹ ውስጥ ያሉ አረፍተ-ነገሮች እርስበርሳቸው የሚደጋገፉ፣ ቀድሞ የሚመጣው አረፍተ-ነገር ለቀጣዩ ፍንጭ የሚሰጥ መሆን እንዳለበት Trimmer እና James (1988) ያስረዳሉ።

### 2.1.7.7 የአንቀጽ አንድነት

የአንቀጽ አንድነት ሲባል በአንቀጹ ውስጥ ባለው መንደርደሪያ አረፍ-ተነገር (ኃይለ ቃል) እና በሌሎች ዝርዝር አረፍተ-ነገሮች መካከል የጠበቀ ትስስር አለ ማለታችን ነው። በአንቀጹ ውስጥ ያለ ዝርዝር አረፍተ-ነገሮች የሚያብራሩትና የሚገልጹት ስለኃይለቃለ መሆን አለበት።ከዚህ አኳያም አንድ አንቀጽ ለመመስረት ሲታሰብ በቅድሚያ ኃይለቃለን ወስኖ መነሳት ለአንቀጽ አንድነት ትልቅ ፋይዳ እንዳለው Trimmer እና James (1988) ያብራራሉ።

## 2.2 የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

ሰይድ (1993) "በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የቀረቡትን የጽህፈት ትምህርትይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ-ዘዴ ትግበራ" በሚል ርዕስ የማስተርስ ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ባቀረቡት ጥናት ተማሪዎች በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ጽህፈትን በተግባር እየተለማመዱ እንደማይማሩ የገለጹ ሲሆን በጥናታቸው ውጤት ማጠቃያያ ላይ የጽህፈት ትምህርት ተግባር ዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንድሚገኝ አመልክተዋል። በመሆኑም የተመራማሪው ጥናት በዘጠነኛ ክፍል የጽህፈት ትምህርት አተገባበር ላይ ስለሚያተኩርና የዚህ ጥናት የሚያተኩረው የጽህፈት ችሎታን በንጽጽር በተግባር በመፈተሽ ችግሮችን ለይቶ የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብ ላይ ስለሆነ፤ እንዲሁም በክፍል ደረጃ፣ ጊዜና ቦታ ጋር አይገናኝም።

አለማየሁ (1998) "አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሁለት የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት" በሚል ርዕስ የማስተርስ ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ባቀረቡት ጥናት ንጽጽራዊ በሆነ መልኩ በግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች በመንግስት ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከሚማሩ ተማሪዎችበ ጽህፈት ረገድ የተሻለ መሆናቸውን ሲገልጹ የመፍትሄ ሀሳብ ብለው ያቀረቡት ከግል ትምህርት ቤት ይልቅ በመንግስት ትምህርት ቤት ያለ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ጽህፈትን አስመልክቶ ለተማሪዎች ተገቢ ትምህርት ሊሰጧቸው እንደሚገባ አመልክተዋል።በመሆኑም የአለማየሁ ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት በማጥናቱ ነው። ነገር ግን የዚህን ጥናት የሚለየው እሳቸው በ11ኛ ክፍል በሚማሩ የግልና የመንግስት ትምህርት ቤት ተማሪዎች መካካል ያለውን የጽህፈት ክሂል ችሎታ በማነጻጸር ውጤቱን ለማሳየት ሞክረዋል፡፡ የዚህ ጥናት ግን በብሁለተኛ ክፍል ደረጃ በአስረኛ ክፍል አፊ ፊትና ኢ-አፊ ፊት አስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ስለሚያተኩርና የሚጠናው ጥናት፣ በክፍል ደረጃ፣ ጊዜና ቦታ በጣም የተራራቀ በመሆኑ ከሳቸው ጥናት የተለየ ጥናት ያደርገዋል።

ጌታቸው (2001) "በደብረ ማርቆስ ከተማ የሚገኙ የ8ኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት" በሚል ርዕስ የማስተርስ ኤም.ኤ ዲግሪ ማሟያ ጥናታቸውን ያቀረቡ ሲሆን በደብረ ማርቆስ ከተማ በሶስት የመንግስት ትምህርት ቤቶች ከሚማሩ 8ኛ ክፍል ሴትና ወንድ ተማሪዎች መካከል በጽሁፍ ክሂል ችሎታ የትኞቹ እንደሚሻሉ ለማጥናት ሞክረዋል። በመሆኑም ተማሪዎችን በሎተሪ የናሙና

አመራረጥ ዘዴ በመምረጥ ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግና ተማሪዎችንና መምህራንን የጽሑፍ መጠይቅእንዲሞሉ በማድረግ በ100 ሴትና በ100 ወንድ ተማሪዎች ላይ በተደረገው ጥናት የተገኘው ውጤት አንፃራዊ በሆነ መልኩ ወንድ ተማሪዎች በጽህፃት ክሂሌ የተሻለ መሆኑን በጥናታቸው አመልክተዋል። እንዲሁም ከዚህ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው በጽህፈት ክሂል ንጽጽራዊ ጥናት መሆኑ ካልሆነ በስተቀር በይዘትም ሆነ ይዞ ከተነሳ አላማና ውጤት ጋር በምንም መልኩ የሚገናኝ አይደለም። ምክንያቱም የእሳቸው ጥናት የሚያተኩረው በደብረ ማርቆስ ከተማ ውስጥ የሚገኙ 8ኛ ክፍል የሴትና ወንድ ተማሪዎች ንጽጽራዊ በመሆኑ ይመሳሰላል። ነገር ግን የዚህ ጥናት ደግሞ በክፍል ደረጃ፣ ጊዜና ቦታ በጣም የተራራቀ እንዲሁም ፆታዊ ልዩነት መሰረት ያደረገ ጥናት ባለመሆኑ ከእሳቸው ጥናት ይለያል።

# ምዕራፍ ሦስት
# 3. የጥናቱ ዘዴ እና አካሄድ

## 3.1 የጥናቱ ንድፍ

ይህ ጥናት ትኩረት የሚያደርገው በዶዮ ሁለትኛ ደረጃ ት/ቤት የአስረኛ ክፍል የሚማሩ ኦሮሚኛ አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት የሆኑ ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት ማድረግ ላይ ነው። አጥኚው መረጃውን ሰብስቦ ገላጭ የምርምር ዘዴን በመጠቀም በዋናነት መጠናዊ ምርምር እና በደጋፊነት አይነታዊ ምርምር ስራ ላይ ውሏል። በዚህ ጥናት አጥኝው ቅይጥ የምርምር ዘዴን የተጠቀመበት ምክንያት ምርምሩ የሚካሄደው በቁጥር መረጃ ትንተናና በገለፃ ስለሆነ ነው። በመሆኑም መጠናዊ ምርምር በቁጥር የመረጃ ትንተና ላይ የተመሠረተ የምርምር አይነት በመሆኑ አጥኝውም በቁጥር ለሚገልጸው የመረጃ ትንተና አመች ሆኖ ስላገኘው ነው። ሌላው በደጋፊነት አይነታዊ ምርምር የተመረጠበት ምክንያት ደግሞ አይነታዊ ምርምር በቁጥር መረጃ ትንተና ላይ የተመሠረተ ሳይሆን በገለፃ ላይ የሚያተኩር ነው። ስለዚህ በቁጥር ከሚተነተነው ውጭ ያለ መረጃ አይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን አቀራረቡ በገላጭ የምርምር ዘዴን ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በመሆኑም አጥኝው ቅይጥ የምርምር ዘዴን የሚከተለውን የCresswell, (2009) እና የያለው (2001) የምርምር መጻሕፍት ለጥናቱ መነሻ ግብዓትነት ተጠቅሟል።

## 3.2 ጥናቱ አካላይ

ይህ ጥናት በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአሥረኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት የሚካሄድ ነው። በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን ማና ወረዳ ዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2016 ዓ.ም በመማር ላይ ካሉት በኦሮሚኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች ተተኳሪነት ነው።

## 3.3 የናሙና አመራረጥ

### 3.2.1 የትምህርት ቤት የናሙና አመራረጥ

የጥናቱ አካላይ የሆኑት በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት በጅማ ዞን ማና ወረዳ ዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ከሚገኙ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ነው። ይህም ት/ቤት የተመረጠበት ምክንያት የአጥኚው መደበኛ የስራ ቦታ እዛው ስለሆነ ጊዜውን ባግባቡ በመጠቀም ውጤታማ ስራ ለመስራት ያስችለው ዘንድ ነው።

### 3.3.2 የክፍል ደረጃ ናሙና አመራረጥ

በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአሥረኛ ክፍል አፍ ፈት እና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ሲሆን ይህም የክፍል ደረጃ በዓላማ ተኮር ሲሆን ይህም የተመረጠበት ምክንያት የአጥኚው የሚያስተምራቸው ክፍሎች ስለሚገኙበት የተማሪዎችን የእውቀት ደረጃ ባግባቡ ስለሚያውቅ ነው።

### 3.3.3 የተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

በመሆኑም በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አስረኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች በድምሩ 348 ሲሆኑ ወንዶቹ 226 ሴቶቹ ደግሞ 122 ናቸው። ከነዚህም መካከል 15 ተማሪዎች አማርኛ አፍ ፈት ሲሆኑ 22 ተማሪዎች ደግሞ ኢ-አፍ ፈት ድምር 37ቱ በዕጣ ናሙና ሲመረጡ 4ቱ ክፍሎች ደግሞ በቀላል የእጣ ናሙና እንዲሁም ሶስቱ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን ደግሞ በጠቅላይ ናሙና ዘዴ ተመርጠዋል።

## 3.4 የጥናቱ መረጃ ምንጮች

የጥናቱ የመረጃ ምንጭ የተማሪዎች የድርሰት አጻጻፍ ስህተቶችና ፍላጎት ማጣት ችግሮች በሰነድ ፍተሻ የተገኘ ሲሆን የተጠኝዎች የጽህፈት ክሂል ፈተና እና በተጠኝዎች ከሚሞሉ ጽሑፍ መጠይቅ የሚገኙ የመረጃ ግብዓቶች ናቸው። እንዲሁም የንድፈ-ሀሳባዊ መሠረቶችና የድህረ-ምረቃ ጥናቶች፣ ድረ-ገጽና የተለያዩ የሀገር ውስጥና የውጭ ሀገር የጥናት መጻሕፍት ምርምር እና የተለያዩ ጆርናሎች ላይ በመመስረት ነው። በመሆኑም የሚለጉት መረጃዎች ተጠኝዎች ከፃፉት ድርሰት፣ ከጽሁፍ መጠይቅ፣ ከድህረ-ምረቃ ጥናቶች፣ ድረ-ገጽ፣ ጆርናሎችና የተለያዩ መጻሕፍት ላይ ከተሰበሰቡ በኋላ በአንድ ላይ በአስፈላጊው ቅደም ተከተል ተዘርዝረው የምክንያትና ውጤት ትንተና ተሰጥባቸዋል።

## 3.5 የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የሚባሉት ጥናቱ እውን እንዲሆን ተገቢ መረጃዎች በአግባቡ የሚሰበሰብባቸው መንገዶችን የሚያብራራ ነው። በመሆኑም አጥኚው ለጥናቱ አስፈላጊና ተገቢ ናቸው ያሏቸውን የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ተከትሏል። እነሱም የጽሕፈት ችሎታ ክሂልን የሚመዝኑ የጽሑፍ ፈተና እና በደጋፊነት የጽሑፍ መጠይቅ ናቸው። በመሆኑም ቀጥለን እያንዳንዳቸውን በዝርዝር እንመልከት።

### 3.5.1 የድርሰት መጻፍት እና ድርሰታቸውን መመርመር

የችሎታ መለኪያ ፈተና ስርዓተ-ትምህርቱን መሠረት ያደረገ መሆን አለበት። "የችሎታ መለኪያ ፈተና መሠረት የሚያደርገው የተዘጋጀ ስርዓተ-ትምህርትን፣ የመማሪያ መጻሕፍትንና የትምህርት ፕሮግራሞችን ነው" Hughes (2003,12) በማለት ሀሳቡን

ያጠናክሩታል። በተጨማሪም ይህ የፈተና አይነት መመስረት ያለበት ባለፈው የክፍል ልምምድ ላይ ሲሆን የመማር ማስተማሩ አንድ አካል ተደርጎ መታየት አለበት፡፡ አላማውም የትምህር ልምዶች ምን ያህል ውጤታማ እንደሆኑ ለመለየት ነው። ስለዚህ ይህ ጥናትም መሠረት ያደረገው ተማሪዎች ቀደም ሲል የተማሩትንና የተለማመደትን የጽህፈት ክሂል ችሎታ ምን ደረጃ ላይ እንደደረሰ ማወቅ ስለሆነ የቀረበው የጽሕፈት ፈተና የችሎታ መለኪያ ፈተና ነው።በዚህም መሠረት ተማሪዎች የተሰጧቸውን ርዕሶች መነሻ አደርገው አንዱን በመምረጥ በተሰጣቸው ጊዜ ውስጥ ድርሰት እንዲጽፉ ተደርጓል።

**ሰንጠረዥ 1. ድርሰት እንዲጽፉ የተደረጉ ተማሪዎች ብዛት**

| አስረኛ ክፍል ተማሪዎች | የተመረጠው ናሙና ብዛት | ፆታ | | ተጽፈው የተመለሱ ድርሰቶች ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| | | ወ | ሴ | |
| አማርኛ አፍ ፈት | 15 | 8 | 7 | 15 |
| አማርኛ ኢ-አፍ ፈት | 22 | 17 | 5 | 22 |

በሰንጠረዡ የቀረበው መረጃ በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ አስረኛ ክፍል የሚማሩ ተማሪዎች ለጥናቱ በጥቅል ናሙና የተሳተፉ የመረጃ ሰጪ ተማሪዎች ዝርዝር ነው። በመሆኑም በዶዮ ሁለተኛ ደረጃ አስረኛ ክፍል የሚማሩት ተማሪዎች በድምሩ 348 ሲሆኑ ወንዶቹ 126 ሴቶቹ ደግሞ 122 ናቸው። ከነዚህም መካከል 15 ተማሪዎች አማርኛ አፍ ፈት ሲሆኑ 22 ተማሪዎች ደግሞ ኢ-አፍ ፈት በድምሩ 37 ተማሪዎች በናሙናነት ተወሰዱ ናቸው።

### 3.5.1.1 የድርሰት መጽሐፍ ርዕሶች መረጣ እና አስተራረም

ተጠኝ ተማሪዎች የጽሕፈት ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንዳለ ለማወቅ ድርሰት እንዲጽፉ ፈተና ተዘጋጅቶላቸዋል። በመሆኑም ተማሪዎቹ ከቀረቡላቸው አስር ርዕሶች መካካል አንዱን በመምረጥ ነፃ የአፃፃፍ ስሌትን ተከትለው ድርሰት ጽፈዋል። የተመረጡት ርዕሶች የተማሪዎችን የቀደመ የጽህፈት ልምድ ከግምት ውስጥ ያስገቡ የትምህርት ደረጃና መርሃ-ትምህርቱን መሠረት ያደረጉና ከአካባቢያቸው ነባራዊ ሁኔታ ጋር የተዛመዱ ናቸው። ርዕሶቹ በሚያስተምሯቸው መምህራንና በጥናቱ አማካሪዬ ተገምግመው አስተያየትና ማሻሻያ ከተሰጠባቸው በኋላ የተመረጡ ናቸው። አስር ርዕሶች የሆኑበት ምክንያት ተማሪዎች በይበልጥ የሚያውቁትን ርዕስ መርጠው እንዲጽፉ ታስቦ ነው። ተማሪዎቹ በመረጡት አንድ ርዕስ ከ150-350 የሚደርሱ ቃላት በተሰጣቸው 90 ደቂቃዎች በመማሪያ ክፍላቸው ውስጥ ድርሰት ጽፈዋል። ድርሰቱንም

እንዲጽፉ የተደረገው አንድ ጊዜ ሲሆን 90 ደቂቃዎች ውስጥ በመረጡት ርዕስ ድርሰት እንዲጽፉ ተደርጓል። በክፍለ ውስጥ እንዲጽፉ የተደረገውም ተማሪዎቹ በሌሎች ሰዎች እንዳያስጽፉና በጥናቱ ላይ ተጽዕኖ እንዳያስከትል በማሰብ ነው።

### 3.5.1.2 የጽህፈት ፈተናው አስተራረም

በዚህ ጥናት የተጠኝዎቹን የጽህፈት ችሎታ በአስተማማኝ መልኩ ለመለካት ያስችል ዘንድ ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶች ሲታረሙ ስሜታዊነት እንዳይንፀባረቅባቸው አስፈላጊው ሁሉ ጥንቃቄ ተደርጓል። በመሆኑም ይህን ስሜታዊነት ለመቀነስና የእርማቱን ስራ የበለጠ አስተማማኝ ለማድረግ የአራሚዎቹ ቁጥር ሶስት ናቸው። ተማሪዎቹ የፃፉት ድርሰት ለአራሚዎች የተሰጡት እያንዳንዱ ድርሰት በሶስት ቅጂ ከተባዛ በኋላ ነው። የማረሚያ መስፈርቶቹም ከተፃፉት ድርሰቶች ጋር በማያያዝ ለአራሚዎቹ ተሰጥቷል። አራሚዎቹ የተገለገሉባቸው የማረሚያ መስፋርቶቹ የHeaton (1990)ን የስህተት ቆጠራ ዘዴን መነሻ በማድረግ ነው፡፡ በመሆኑም አራሚዎቹ ድርሰቶቹን ሲያርሙ በቅድሚያ ምን ምን መመዘኛ ነጥቦችን መመልከት እንዳለባቸው በምዕራፍ ሁለት በተጠቀሱት ክለሳ ድርሳናት ጽሁፎች ላይ በመመስረት የማረሚያ መመሪያና የድርሰት መመዘኛ ነጥቦች ከሚታረመው ድርሰት ጋር አብሮ ተሰጥቷቸዋል።

### 3.5.1.3 የጽሑፍ መጠይቅ

ለተማሪዎች የቀረበው የጽሑፍ መጠይቅ በምዕራፍ ሁለት ውስጥ የተነሱትን ጽንሰ-ሀሳቦች መሠረት በማድረግ የተዘጋጁ ናቸው። መጠይቁ በድርሰት ፈተና የተገኘውን መረጃ የበለጠ ለማረጋገጥ፣ ለማጠናከርና ተጨማሪ መረጃን ለማግኘት ታስቦ ተግባራዊ የሆነ ነው። የጽሑፍ መጠይቁም ሶስት ክፍልች አለት። የመጀመሪያው ክፍል ስለመጠይቁ መግለጫ፤ የሁለተኛው ክፍል መጠይቁን ስለሚሞላው ግለሰብ አስፈላጊ የሆኑ አጠቃላይ መረጃዎችን ለማግኘት የሚያስችል ክፍል ሲሆን ሶስተኛው ክፍል ደግሞ የጽህፈት ትምህርትን በተመለከተ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን የሚይዝ ነው።

## 3.6 የመረጃ አተናተን

### 3.6.1 የጽህፈት መረጃ አተናተን

ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶች በሶስት አራሚዎች ከታረሙ በኋላ የሚታዩት ስህተቶች ማለትም የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም፣ የአረፍተ ነገር አወቃቀር፣ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም፤ የአንቀጽ አደረጃጀት፣ የፊደል አጣጣልና አጠቃቀም ወዘተ. ቀደም ሲል በተጠቀሱት የስህተት አይነቶች ስር እንደየስህተት አይነታቸው ተመዝግበዋል። ድርሰቱ ሲታረም አስተማማኝ እንዲሆን ለአንድ ተማሪ የሚመዘገበው ስህተት የሶስቱን

አራሚዎች አማካኝ ውጤት በመውሰድ ነው። ቀጥሎም የጥናቱ ተሳታፊ የሆኑ አማርኛ አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የፃፏቸውን ድርሰቶች የቃላት ብዛት በመቁጠር በድርሰቶቹ ብዛት ይካፈላል። ከዚያም የአንድ ተማሪ ድርሰት በአማካኝ የፃፈባቸው የቃላት ብዛት ይታወቃል። ከዚያም አማካኝ ስህተቱን ለአማካኝ ቃላት በማካፈልና በ100 በማባዛት በአንድ ድርሰት ውስጥ የሰሩት ስህተቶች በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። በዚህ ስሌት መሠረት አማርኛ አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የፃፏቸውን ድርሰቶችን በማነፃፀር ትንተናው ተካሄዷል። ስለዚህም ይረዳ ዘንድ በድርሰቶቹ ውስጥ ያለውን አማካይ የቃላት መጠን፣ አማካይ ስህተት፣ አማካይ የስህተት ድግግሞሽ ለማሳየት ሲባል Kroll (1990), *Kenworthy* (2006), *Staples* እና *Randi* (2016) የተጠቀሙበት ዘዴ ተግባራዊ ተደርጓል። የስሌት ቀመሩም እንደሚከተለው ነው።

$$\text{አማካይ የቃላት መጠን} = \frac{\text{ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶች ቃላት ብዛት}}{\text{የተፃፉት ድርሰቶች ብዛት}}$$

$$\text{አማካይ ስህተት} = \frac{\text{አጠቃላይ የስህተት ብዛት}}{\text{የተፃፉት ድርሰቶች ብዛት}}$$

$$\text{አማካይ የስህተት ድግግሞሽ መጠን} = \frac{\text{አማካይ የስህተት ብዛት} \times 100}{\text{ለአማካይ ቃላት}}$$

በመሆኑም አጥኝው በምዕራፍ አራት ላይ ለመረጃ ትንተና ከላይ የቀረበውን ቀመር ተግባራዊ በማደረግ እና ምዕራፍ ሁለት ክለሳ ድርሳን ላይ የቀረቡትን ንድፈ ሀሳቦች ጋር በሚዋሀድ መልኩ ከድርሰቶቹ በተገኙትና ከጽሑፍ መጠይቅ በተገኙት መረጃዎች ላይ ትንተና ተሰጥቶባቸዋል።

### 3.6.2 የጽሁፍ መጠይቅ አተናተን

የጽሁፍ መጠይቁ ጠቀሜታው በተግባር በፃፉት ድርሰት ላይ የታዩት ስህተቶችና በጽሑፍ መጠይቁ የመለሱት ምን ያህል እውነታ እንዳለውና እንደሌለው በንጽጽር ለማየት ይጠቅማል።የጽሑፍ መጠይቁ ዝግ መጠይቅን የተከተለ ሲሆን ለትንተና የቀረቡት አራት አማራጮችን የያዙ 10 ጥያቄዎች ናቸው። አራት አማራጭ የሆነበት ምክንያት የመካከለኛው ለመወሰን እቸገራለሁ የሚለው አማራጭ ከየትኛውም ጋር መደመር ስለማይችል ለጥናቱ አስፈላጊ ሆኖ ስላልተገኘ ነው።

በመሆኑም አራቱ አማራጮች በጥናቱ ወደ ሁለት በመክፈል ማለትም ፈጽሞ አልስማማምና አልስማማም ውጤታቸው ተመሳሳይ በመሆኑ በአንድ ላይ ተድምረዋል። እንዲሁም በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ በአንድ ላይ ተደምረው በእያንዳንዱ ጥያቄ ምላሽ የሰጡ ተጠኝዎች ብዛት ለጠቅላላ መላሾቹ ብዛት ተካፍሎ በመቶኛ በማስላት አማርኛ አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ለብቻ ተለይቶ በጥቅልና በጾታ ንጽጽራዊ ጥናት በማድረግ ትንተናው ተካሄዷል።

# ምዕራፍ አራት

# 4. የመረጃ ትንተና

በዚህ ምዕራፍ በናሙና ከተመረጡ ተማሪዎች የተሰበሰቡ መረጃዎችን በመተንተን በምዕራፍ አንድ ላይ ለቀረቡት ጥያቄዎች መልስ ተሰጥቶባቸዋል። በዚህም መሠረት አማርኛ ቋንቋ አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶች በምዕራፍ ሁለት Pincas (1982) እና Heaton (1990)ን በመጥቀስ የቀረበውን የጽህፈት ችሎታ መመዘኛ ነጥቦችን መሠረት በማድረግ የተሰበሰበው የድርሰት መረጃና የጽሁፍ መጠይቅ መረጃ እንደሚከተለው ንጽጽራዊ ትንተና ተሰጥቶባቸዋል።

## 4.1. የቃላት አጠቃቀም

አማርኛ ቋንቋ አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የፃፏቸው ድርሰቶችን በማረም የታዩትን የቃላት አጠቃቀም ስህተቶች ለመቁጠር ተሞክሯል። እንደ ስህተት የተመዘገበው ከዚህ በታች የቀረበውን ይመስላል።

ሰንጠረዥ 2. የተጠኝ ተማሪዎች የቃላት አጠቃቀም ችሎታን በተመለከተ ከፃፉት ድርሰት የተገኘ ውጤት

| የስህተት አነይት | አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች | | | | | | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቃላት አጠቃቀም | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | የስህተት አማካይ | ስህተት በመቶኛ | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | የስህተት አማካይ | ስህተት በመቶኛ |
| | 15 | 2625 | 175 | 462 | 30.8 | 17.6% | 22 | 2,835 | 128.36 | 1,278 | 58 | 45.5% |

ከሰንጠረዥ 3. መመልከት እንደሚቻለው የቃላት አጠቃቀምን በተመለከተ አማርኛ አፈ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች 2625 ቃላትን የተጠቀሙ ሲሆን በድርሰቶቹ ውስጥ 462 ቃላት በስህተትነት ተቆጥረው ተመዝግበዋል። እንዲሁም አማርኛ ኢ-አፈ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች 2835 ቃላትን የተጠቀሙ ሲሆን በድርሰቶቹ ውስጥ 1278 ቃላት በስህተትነት ተቆጥረው ተመዝግበዋል። ከዚህ አንፃር አማርኛ ቋንቋ አፈ ፈት ተማሪዎች የተመዘገበባቸው ስህተት መጠን አማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍ ፈት ከሆኑት ተማሪዎች ያነሰ ስለሆነ የተሻለ የቃላት አጠቃቀም ችሎታ አላቸው ማለት ይቻላል። በመቀጠል አንድ ድርሰት የተፃፈበትን አማካይ ቃላት ብዛት ለማወቅ የተቆጠረውን የቃላት ብዛት ከድርሰቶቹ ቁጥር ጋር በማካፈል ማወቅ ተችሏል። በዚህም

መሠረት አማርኛ አፊ ፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ያለትን 2625 ቃላት ለጠቅላላ ድርሰቶቹ ለ15 ድርሰቶች) ስናካፍለው የአንድ ተማሪ ድርሰት በአማካኝ 175 ቃላት የተፃፈ መሆኑን ማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም የተመዘገቡትን ስህተቶች አማካይ ለማወቅ በስህተት የተመዘገቡትን ቃላት ለተፃፈው ድርሰት ብዛት ስናካፍለው 30.8 በእያንዳንዱ ድርሰት ውስጥ የተመዘገበ አማካይ ስህተት መሆኑ ታውቋል። ከዚህ በኋላ አማካይ ስህተቱን ለአማካይ ቃላት በማካፈልና በ100 በማብዛት የተመዘገበውን ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ተችሏል።

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \left|\frac{42.18}{175} \times 100 = 24.1\%\right|$$

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \left|\frac{30.8}{175} \times 100 = 30.5\%\right|$$

እንዲሁም አማርኛ ኢ-አፍ ፍት ተማሪዎች የፃፏቸውን ድርሰቶች አማካይ የቃላት ብዛት ለማወቅ ድርሰቶቹ የተፃፉበትን አጠቃላይ የቃላት ብዛት በመቁጠር ለድርሰት ቁጥሩ በማካፈል ማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት በአማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች የተፃፉት ድርሰቶች 2.835 ቃላት ሲኖራቸው ይህ ቁጥር ለ22 ድርሰቶች ሲካፈል አንድ ድርሰት በአማካይ በ128.36 ቃላት የተፃፈ መሆኑን ተረጋግጧል። በተጨማሪም በስህተትነት የተመዘገቡትን ቃላት ቁጥር ለድርሰቶቹ በማካፈል አማካይ ስህተትን ለማወቀ ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት በስህተትነት የተመዘገበው 1278 ሲካፈል ለ22 ድርሰቶች አንድ ድርሰት በአማካይ በ58 ቃላት ስህተት በእያንዳንዱ ድርሰት ውስጥ መመዝገቡ ተረጋግጧል። በመቀጠል የተፈፀመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ እንደሚከተለው ተሰልቷል።

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \left|\frac{64.05}{106.75} \times 100 = 60.4\%\right|$$

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \left|\frac{58}{128.36} \times 100 = 45.5\%\right|$$

ከላይ ከተገኘው ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍ ፊትና ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ደርሰቶች ውስጥ የተመዘገቡት ስህተቶች ሲነፃፀሩ አማርኛ አፍ

ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ 17.6% ያህል የቃላት አጠቃቀም ስህተት እንዳለባቸውና አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ደግሞ 58% ያህል ስህተት እንዳለባቸው የተገኘው ውጤት ያሳያል። ከዚህም አንፃር አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች አነስተኛ ስህተት ስለተገኘባቸው በቃላት አጠቃቀም ችሎታ የተሻሉ ናቸው ማለት ይቻላል።

ሰንጠረዥ 3. የተጠኙ ተማሪዎች የቃላት ምርጫን በተመለከተ መምህራን ያስተምሯቸው እንደሆነ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ መረጃ

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ /በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | መቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍ ፈት | አማርኛ አፍ ፈት | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት |
| የትምህርት ክፍል መምህራን በጽህፈት ወቅት ስለምጠቀሙባቸው የተለያዩ የቃላት ምርጫ አስተምረውኛል | ፈጽሞ አልስማማም | 0 | 0% | 0 | 0% |
| | አልስማማም | 3 | 20% | 3 | 13.63% |
| | እስማማለሁ | 8 | 53.33% | 18 | 81.81% |
| | በጣም እስማማለሁ | 4 | 26.66% | 1 | 4.54% |

ከላይ ከቀረበው መረጃ ለመረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ውስጥ 20% የሚሆኑት መምህራን በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ስለ ቃላት አመራረጥ ሲያስተምሩ የቃላት አጠቃቀምና ምርጫን እንደሚያስተምሯቸው 20% የሚሆኑት አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች በ22 ደግሞ እንደማያስተምሯቸው በሰጡት የጽሐፍ መጠይቅ ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል። በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ውስጥ 81.81% የሚሆኑት መምህራን በጽህፈት ትምህርት ወቅት ስለሚጠቀሙባቸው የቃላት አጠቃቀምና ምርጫ እንደሚያስተምሯቸው የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 13.63% የሚሆኑት ደግሞ መምህራን በጽህፈት ትምህርት ወቅት የቃላት አጠቃቀም ምርጫን እንደማያስተምሯቸው የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍ ፈትም ሆነ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች አብዛኞቹ እንደገለጹት መምህራን የቃላትን አጠቃቀምና ምርጫ እንደሚያስተምሯቸው ነው።

ነገር ግን ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እና በተግባር በደርሰቶቻቸው የታየው ተመሳሳይ ነው ለማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ከላይ በሰንጠረዥ 4 በቀረበው የድርሰታቸው መረጃ ውጤት መሠረት 50% የሚሆን የቃላት አጠቃቀም ስህተት ሲታይባቸው አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ደግሞ በፃፉት ድርሰት 60%

የሚሆን ስህተት ታይቶባቸዋል።በመሆኑም የሰጡት የጽሐፍ መጠይቅ ምላሽ መምህራንን ከመፍራት አኳያ የመለሱት ሊሆን ይቻላል ከዚህ አንፃር የተሰጠው ምላሽ ከድርሰቶቻቸው ጋር ተያዥነት ያለውና ተገቢ ነው ማለት አይቻልም፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ አማርኛ አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የቃላት አጠቃቀም ችግሮች ከሚገኙባቸው አረፍተ-ነገሮች ለአብነት ያህል በማሰረጃነት ለማቅረብ ተሞክሯል። በአረፍተ-ነገሮቹ ውስጥ ጎላ ብለው ከሚስተዋሉ ስህተቶች አንፃር በመመልከት እንጂ በእያንዳንዱ አረፍተ-ነገር ውስጥ የሚታየው ስህተት አንድ ብቻ አይደለም።

## 1. የቃላት አጠቃቀም ስህተቶች

### 1.1 አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የቃላት አጠቃቀም ስህተቶች

### ሀ. የቃላት ድግግሞሽ እና ድረታ

- "---HIV አደስ <u>በሽታ</u> <u>ለበሽታ</u> የምያጋልጥ ቫይረስ <u>ነወ</u>
- " "---ህይወት ያላችቸው ነገሮች <u>ሁለ</u> ወሃ <u>ያስፈልጋቸዋል</u>--"
- "---ጫት የምቅሙ ሰዎች ጠንነታቸው <u>ይታወካል</u> <u>ይታመማሉ</u> --"

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎች አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው። በመሆኑም የቀረቡት ምሳሌዎች ያሉባቸው ችግር የቃላት አጠቃቀም ብቻ ሳይሆን የስርዓተ-ነጥብ ችግር፣ የሰዋስው ችግር፣ የፊደል ግድፈትና ወዘተ. ችግሮች አሉባቸው። ነገር ግን ሌሎች ችግሮችን በቦታቸው ስለምናይ ከንዑስ ርዕሱ ጋር የሚሄደውን ችግር ቀጥለን እንመልከት።

በቀረቡት ምሳሌዎች የተሰመሩባቸው ቃላት የቃላት ድግግሞሽና ድረታ የሚታዩባቸው ናቸው። ነገር ግን ተማሪዎቹ በድርሰት ትምህርታቸው ክፍለ ጊዜ በመምህራን ስለቃላት አጠቃቀምና ምርጫ ስለመማራቸው የሰጡት ምላሽ ይህን የሚያፈርስ ነው። "---ኤች አይ ቪ አድስ <u>በሽታ</u> የምያጋልጥ ቫይረስ <u>ነው።</u>"

- "--ህይወት ያላቸው ነገሮች <u>ሁሉ</u> ውሃ <u>ያስፈልጋቸዋል።</u> --"
- "---ጫት የሚቅሙ ሰዎች ጤንነታቸው <u>ይታወካል</u>።--"

### ለ. ባዕድ ቃላት አጠቃቀም"

- "--- <u>HIV</u> አደስ በሽታ ለበሽታ የምያጋልጥ ቫይረስ <u>ነወ</u>

- "---ጫት መቃም ውልፍ ያሰይዛል--"
- "--- ያገራችን ህዝቦች ታሪክ ጠንቅቀው ያርፋሉ---"
- "---ማቴሪያሎችን ለማጽዳት ይጥቅማል---
- "ሶሻል ላይፋቸው የለለ ይሆናል--"

ከላይ በምሳሌነት የቀረቡት እና የተሰመረባቸው ቃላት የአማርኛ ቋንቋ ያልሆኑ ባዕድ ወይም የውጭ ቃላት ናቸው። አንድ ቋንቋ መዋስን ብቸኛ አማራጭ የሚያደርገው በቋንቋው መግለጽ የማይችለውን ነገር ነው። ነገር ግን እነዚህ ባዕድ ቃላት በአማርኛ መተኪያ ያላቸውና ቋንቋውም መግለጽ የሚችል ሲሆን ተማሪዎቹ ይህን የመረጡበት ምክንያት የቋንቋ ችግር ስላለባቸው እንግሊዘኛን መጠቀም መርጧል። በመሆኑም እንደሚከተለው ተስተካክለው ቢፃፉ ከባዕድ ቃላት የፀዳ የቃላት አጠቃቀምና ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቁ አረፍተ-ነገሮች ስለሚሆኑ ተደራሲያንን ሊያግባቡ ይችላሉ።

- "--- ኤች አይ ቪ ኤድስ ለበሽታ የሚያጋልጥ ቫይረስ ነው።
- "---ጫት መቃም ሱስ ያሰይዛል።--"
- "--- ያገራችን ህዝቦች ታሪክ ጠንቅቀው ያውቃሉ።---"
- "---ማቁሳቁሶችን ለማጽዳት ይጥቅማል።---"

## 1.2 አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የቃላት አጠቃቀም ስህተቶች

### ሀ. የቃላት ድግግሞሽ እና ድረታ

- "HIV አደስ በሽታ ለበሽታ እምያጋልጥ ቫይረስ ነው"
- "---ህይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ ወሃ ያስፈልጋቸዋለ--"
- "---ጫት የምቅሙ ሰዎች ጠንነታቸው ይታወካል ይታመማሉ --"
- ሶሻል ላይፋቸው የለለ ይሆናል--"

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎች አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው። በመሆኑም የቀረቡት ምሳሌዎች ላይ የተሰመረባቸው ቃላት የቃላት ድግግሞሽና ድረታ የሚታይባቸው ናቸው። ነገር ግን ተማሪዎቹ በድርሰት ትምህርታቸው ክፍለ ጊዜ በመምህራን ስለ ቃላት አጠቃቀምና ምርጫ ስለመማራቸው የሰጡት ምላሽ ይህን የሚያፈርስ ነው። በትክክል የተማሩ ቢሆን ኖሮ በምሳሌዎቹ ላይ የቀረቡትን ስህተቶች አይፈጽሙም ነበር። ስለዚህ መምህራን ስለቃላት አጠቃቀምና

ምርጫ አስተምረውናል ያሉትን ከጥናቱ አንፃር የምንረዳው በሁለት መንገድ ነው። የመጀመሪያው መምህራንን ከመፍራት የመለሱት ሊሆን ይችላል። ሁለተኛው ደግሞ በዘፈቀደ መልስ የመስጠት ብቻ ብለው የመለሱት ሊሆን እንደሚችል አጥኝው ይገምታል። በመሆኑም እንደሚከተለው ተስተካክለው ቢፃፉ የቃላት አጠቃቀምና ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቁ አረፍተ-ነገሮች ስለሚሆኑ ተደራሲያንን ሊያግባቡ ይችላሉ።

- ❖ ኤች አይ ቪ አድስ ለበሽታ የሚያጋልጥ ቫይረስ ነው።"
- ❖ "---ህይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ ወሃ ያስፈልጋቸዋል።--"
- ❖ "---ጫት የምቅሙ ሰዎች ጤንነታቸው ይታወካል ይታመማሉ። --"
- ❖ ሶሻል ላይፉቸው የለለ ይሆናል።--"

## ለ. ባዕድ ቃላት አጠቃቀም

- ❖ "---ሰዎች ሃክም በት ሂደው ቸክ መደረግ አለባቸው---"
- ❖ "---ታብለት ሳያቋርጡ ብየቀኑ መወስደ አለባቸው፡፡"
- ❖ "---ጫት መቃም ስታየላቸወ አርግው ይወስዳሉ"

ከላይ በምሳሌነት የቀረቡት እና የተሰመረባቸው ቃላት የአማርኛ ቋንቋ ያልሆኑ ባዕድ ወይም የውጭ ቃላት ናቸው። አንድ ቋንቋ መዋስን ብቸኛ አማራጭ የሚያደርገው በቋንቋው መግልጽ የማይችለውን ነገር ነው። ነገር ግን እነዚህ ባዕድ ቃላት በአማርኛ መተኪያ ያላቸውና ቋንቋውም መግለጽ የሚችል ሲሆን ተማሪዎቹ ይህን የመረጡበት ምክንያት የአማርኛ ቋንቋ ቃላት ችግር ስላለባቸው እንዲሁ መረዳት አያዳግትም። በመሆኑም እንደሚከተለው ተስተካክለው ቢፃፉ ከባዕድ ቃላት የፀዱ የቃላት አጠቃቀምና ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቁ አረፍተ-ነገሮች ስለሚሆኑ ተደራሲያንን ሉሊግባቡ ይችላሉ።

- ❖ "---ሰዎች ሃኪም ቤት ሂደው ቼክ መደረግ አለባቸው።---"
- ❖ "---ክኒን ሳያቋርጡ ብየቀኑ መወስደ አለባቸው፡፡"
- ❖ "---ጫት መቃም መለያ ባህሪያቸው አርግው ይወስዳሉ።"

## 4.2. የአረፍተ-ነገር ሰዋሰዋዊነት

በዚህ ክፍል ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚታዩ ሰዋስዋዊ ስህተቶችን በመቁጠር የሚከተለው መረጃ ተተንትኗል።

ከላይ የተገለጹት ስህተቶች ለአሰራር ያመቹ ዘንድ በአንድ ከፍል በመመደብ ትንተና ተደርጓል።ስህተቶች ማለትም የፆታ፣ የቁጥር፣ የመደብ አጠቃቀም፣ የቃላትና ሀረጋት ቅንብሮችን በተመልከተ ነው።

ሰንጠረዥ 4 የተጠኝዎች አረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታ በተመለከተ ከድርሰቶቻቸው የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| የስህተት አይነት | አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች | | | | | | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቃላት አጠቃቀም | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አምካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | አማካይ ቃላት | የስህተት ብዛት | አምካይ ስህተት | ስህተት በመቶኛ |
| | 15 | 2,625 | 175 | 75 | 5 | 2.85% | 22 | 2.835 | 128.86 | 201 | 9 | 7% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ 75 የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ስህተቶች ሲቆጠሩ አማርኛ ኢ-አፈ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ደግሞ 201 ስህተቶች ተቆጥረዋል። በመቀጠል የስህተቱን መጠን በመቶኛ ለማወቅ ከዚህ በፊት የተሰራበትን ቀመር ተግባራዊ በማዴድረግ ለማስላት ተሞክሯል። በዚሁም መሠረት አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የፈጸሙት አማካይ ሰዋስዋዊ ስህተትን ማወቅ ስለሚያስፈልግ በስህተትነት የተመዘገቡትን ከድርሰት ቁጥር ጋር በማካፈል አማካይ የስህተት መጠኑን ለማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት 75 ለ15 ስናካፍለው 5 አማካይ ስህተት እናገኛለን። ተማሪዎቹ ድርሰት የፃፈባቸው አማካይ ቃላት ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለፀው 175 መሆኑ ይታወቃል። በመቀጠል የተፈጸመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ እንደሚከተለው ተሰልቷል።

$$\frac{\text{አማካይ ስህተት}}{\text{አማካይ ቃላት}} \times 100 \quad \Big| \quad \frac{5}{175} X 100 = 2.85\% \Big|$$

በሌላ በኩል አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚገኘውን ስህተት በመቶኛ ለማወቅ ከላይ በቀረበው መልኩ ተሰልቷል። በመሆኑም ተማሪዎቹ በፃፉት ድርሰት ውስጥ 201 የሚሆኑ የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ስህተቶች ተቆጥረው ተመዝግበዋል። የስህተቱን አማካይ ለማወቅ ደግሞ ስህተቶቹን ለድርሰቱ ቁጥር በማካፍል ማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት 201 ለ22 ሲካፈል 9 አማካይ ስህተት

መሆኑ ተረጋግጧል። ድርሰት የፃፉበት አማካይ ቃላት ቀደም ሲል እንደተገለፀው 128.86 ነው። በመቀጠል የተፈፀመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ እንደሚከተለው ተሰልቷል። <u>አማካይ ስህተት</u> × 100 | <u>9</u> X 100 = 7% |

አማካይ ቃላት 128.86

ከላይ ባሉት የጥናት ውጤቶች መረዳት እንደተቻለው አማርኛ አፊ ፊት ተማሪዎች 3.79% ሰዋስዋዊ ስህትት ሲገኝባቸው አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች ደግም 7% ሰዋስዋዊ ስህትት ተገኝቶባቸዋል በመሆኑም በሰዋስዋዊ የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታቸው አማርኛ አፍ ፊት ተማሪዎች ከኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች የተሻሉ እንደሆነ ያስመዝገቡት ስህተት ያመለክታል።

ሰንጠረዥ 5 ተጠኝዎች ድርሰት ሲጽፉ የአረፍተ-ነገር አወቃቀር ችሎታቸውን በተመለከተ በጽሁፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ በ/ፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | መቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍ ፊት | አማርኛ አፍ ፊት | አማርኛ ኢ-አፍ ፊት | አማርኛ ኢ-አፍ ፊት |
| ድርሰትን ስጽፍ ሰዋስውን በአግባቡ እጠቀማለሁ | ፈጽሞ አልስማማም | 1 | 6.66% | 0 | 0% |
| | አልስማማም | 2 | 13.335% | 3 | 14% |
| | እስማማለሁ | 11 | 73.33% | 14 | /64.82% |
| | በጣም እስማማለሁ | 1 | 6.66% | 4 | 19.18% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት አንደሚቻለው ከአማርኛ አፊ ፊት ተማሪዎች ውስጥ 80% የሚሆኑት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ ሰዋስውን በአግባቡ እንደሚጠቀሙ የገለጹ ሲሆን 20% የሚሆኑት አማርኛ አፍ ፊት ተማሪዎች ደግሞ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ ሰዋስውን በአግባቡ እንደማይጠቀሙ የሰጡት መረጃ ያመለክታል።

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች ውስጥ 86% የሚሆኑት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ ሰዋስውን በአግባቡ እንደሚጠቀሙ የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 15% የሚሆኑት ደግሞ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ ሰዋስውን በአግባቡ እንደማይጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያሳያል። ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍ ፊትም ሆኑ ኢአፍፆት ተማሪዎች አብዛኞቹ እንደገለጹት

መምህራን በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ ሰዋስውን በአግባቡ እንደሚጠቀሙ መግለፃቸውን በጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል። ነገር ግን ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እና በተግባር በድርሰቶቻቸው የታየውን ተመሳሳይነት አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ከላይ በሰንጠረዥ 8 የሰጡት መረጃ ከአፍ ፈት ተማሪዎች አንፃር ተዓማኒነት አለው ለማለት ያስችላል። ምክንያቱም አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ከኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የተሻሉ የሰዋስው አጠቃቀም ችሎታ እንዳላቸው ከጥናቱ መረዳት ተችሏል። ነገር ግን አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ ትክክል እንዳልሆነ ከድርሰቶቻቸው የተገኘው መረጃ ያሳያል።

ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ አማርኛ ኢ-አፍ ፈትና አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የአረፍተ-ነገር አወቃቀር (ሰዋስው) ችግሮች ከሚገኙባቸው አረፍተ-ነገሮች ለአብነት ያህል በማሰረጃነት ለማቅረብ ተሞክሯል። በአረፍተ- ነገሮቹ ውስጥ ጎላ ብለው ከሚስተዋሉ ስህተቶች አንፃር በመመልከት እንጂ በእያንዳንደ አረፍተ-ነገር ውስጥ የሚታየው ስህተት አንድ ብቻ አይደለም።

## 2. የሰዋስው ስህተቶችሀ. የቁጥር ስምምነት ችግር

### 2.1. አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የሰዋስው ስህተቶች

### ሀ. የቁጥር ስምምነት ችግር

- ''ህይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ ውሃ አስፈላጊ ናቸው"
- "አፈር ቅዳ ቅዳምውን ቦታይይዛሉ"
- "ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች እያጠቃ ናችው"

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎች አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው፡፡ በመሆኑም የቀረቡት ምሳሌዎች የቁጥር ስምምነት ችግር ብቻ ያለባቸው ሳይሆኑ የአረፍተ-ነገር ሰዋስው፣ የስርዓተ-ነጥቦች ችግር፣ የፊደላት ግድፈትና ወዘተ. ችግር ያለባቸው ናቸው። ነገር ግን የተገለጹት ችግሮች በሚፈቅደው ቦታ ወደ ፊት ስለሚነሱ ከላይ የቀረበውን ንዑስ ርዕስ የሚመለከቱትን ብቻ እንመለከት።

በመሆኑም የመጀመሪያው አረፍተ-ነገር ''ህይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ ውሃ አስፈላጊ ናቸው" የሚለው የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ የቁጥር ስምምነት ችግር ይታይበታል። መሆን የነበረበት ውሃ ህይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ አስፈላጊ ነው።" በሚል ተስተካክሎ

ቢፃፍ የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ ችግሮቹ ይቀረፉ ነበር፡፡ ሁለተኛው አረፍተ-ነገር ደግሞ "አፈር ቅዳ ቅዳምውን ቦታይይዛሉ" የሚል ሲሆን ይህ አረፍተ-ነገር የፊደል ግድፈት፣ አላስፈላጊ የቃል ጭማሪ መግባትና የስርዓተ-ነጥብ ችግር አለበት። ነገር ግን ለምሳሌ ከቀረበበት ርዕስ ጋር የሚገናኘው ችግር የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ የቁጥር አለመስማማት ነው። መሆን የነበረበትም አፈር ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል።" በዚህ መንገድ ቢስተካከል ችግሮቹ ይቀረፍ ነበር።

በአጠቃላይ ሁሉም በምሳሌነት የቀረቡት አረፍተ-ነገሮች ከላይ ሁለቱ ምሳሌዎች በቀረቡት መሠረት ሁሉም ተመሳሳይ ችግሮች ያሉባቸው አረፍተ-ነገሮች ናቸው። በመሆኑም እንደሚከተለው ተስተካክለው ቢፃፉ የቃላት አጠቃቀምና ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቁ አረፍተ- ነገሮች ስለሚሆኑ ተደራሲያንን ሊያግባቡ ይችላሉ።

- ''ህይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ ውሃ አስፈላጊ ነው።"
- "አፈር ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል።"
- "ሁሉንም የህብረተሰብ ክፍሎች እያጠቃ ነው።"

### ለ. የመደብ አጠቃቀም ችግር

ኦሮሚኛ አፍ ፈት እና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የመደብ አጠቃቀም ችግሮች ታይቶባቸዋል። ይህም የሚያሳየን በድርሰት አፃፃፍ አይሳሳቱም ማለት ሳይሆን ድርሰቱን የፃፉት በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በመሆኑ ሊሆን ይችላል፡፡ በአፍ መፍቻ ቋንቋቸው በንግግር ጊዜ የመደብ አጠቃቀምን በደንብ አውቀው ስለሚጠቀሙት በድርሰታቸውም ይህ ሁኔታ ጠቅሟቸዋል ማለት ይቻላል።

### ሐ. የቃላት ቅደም ተከተል ችግር

የቃላት ቅደም ተከተል ችግር ማለት አንድ ቃል በተገቢው ቦታና የሚገባበትን የቦታ ቅደም ተከተል ሳይጠብቅ መጠቀም ማለት ነው።

- "የተፈጥሮ ሃብቶች ከምባሉት ምካከል ቀዳምውን ቦታ አፈር ይይዛል
- "ይዎት ላላቸው ነገር አስፈላጊ ሁሉ ዉሃ ንው።"
- "ነጭ የደም ሰል እማዳከም የሰውነት ሰውነ የበሽታአቅም መክላከያ ያሳጣል"
- ''ጫት መቃም ጉዳት ያስከትላል ጥና ላይ።"

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎች አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው። በመሆኑም የቀረቡት ምሳሌዎች የተለያዩ የሰዋስው ችግር

ያሉባቸው ናቸው።ነገር ግን ከላይ የቀረበውን ንዑስ ርዕስ የሚመለከቱትን ብቻ እንመልከት።

በመሆኑም የመጀመሪውን ምሳሌ ብናይ የተፈጥሮ ሃብቶች ከምባሉት ምካከል ቀዳምውን ቦታ አፈር ይይዛል" የሚለው አገላልጽ ለንግግር ቢሆን ሊያግባባ ይችላል። ምክንያቱም የቋንቋ አቀባይና ተቀባይ አብረው መልዕክቱን ስለሚቀባበሉ ማስተካከያ በማድረግ መልዕክቱን መረዳት ይቻላል። ነገር ግን በጽህፈት ጊዜ መልክት አቀባዩና ተቀባዩ አብረው ስለማይገናኙና የቋንቋው ሰዋስው ስለማይፈቅድ በዚህ መልኩ መጠቀም ተገቢ አይደለም።

ከዚህም በተጨማሪ መልዕክቱ በቀላል ለመልዕክት ተቀባዩ እንዳይተላለፍ እክል ይገጥመዋል።ስለዚህ ይህ አረፍተ-ነገር መፃፍ የሚገባው "የተፈጥሮ ሃብቶች ከምባሉት መካከል አፈር ቀዳሚውን ቦታ ይይዛል። በሚል መቅረብ አለበት።

ሁለተኛው አረፍተ-ነገር ደግሞ "ህይዎት ላላቸው ነገሮች ሁሉ ውሃ አስፈላጊ ነው፡፡" የሚለው በሚል ተስተካክሎ ቢፃፍ ሁሉንም ያግባባ ነበር። ሶስተኛው አረፍተ-ነገር የስርዓተ-ነጥብ ችግር፣ አላስላጊ የቃላት ጭመራና የመሳሰሉት ችግሮች ይታይበታል። ሆኖም ከርዕሱ ጋር የሚሄደውን የቃላት ቅደም ተከተል ችግር ስናይ "ነጭ የደም ሰል እማዳከም የሰውነት የበሽታ አቅም መክላከያ ያሳጣል" የሚለው በአረፍተ-ነገሩ መተላለፍ የተፈለገው መልዕክት አገላለጽ ተገቢ አይደለም። ስለዚህ "ነጭ የደም ሴልን በማዳከም የሰውነት የበሽታ መከላከያ አቅምን ያሳጣል" በሚል ተስተካክሎ ቢቀርብ ሁሉንም ተደራሲ ሊያግባባ ይችላል።

- "የተፈጥሮ ሃብቶች ከምባሉት ምካከል አፈር ቀዳምውን ቦታ ይይዛል።"
- "ህይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ ውሃ አስፈላጊ ነው፡፡"
- "ነጭ የደም ሴል በማዳከም የሰውነት የበሽታ መክላከያ አቅም ያሳጣል"
- ''ጫት መቃም ጤና ላይ ጉዳት ያስከትላል።''

## 2.2. አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የሰዋስው ስህተቶች

### ሀ. የቁጥር ስምምነት ችግር

- "አፈር ብዙ ጥቅም አላቸው
- ''ሰዎች ውሃ ለብዙ ነገር ይጠቀማል''

❖ ጫት ጉዳት እንጅ ምንም ጥቅም የላችውም

ከላይ የቀረቡ ምሳላዎች አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው። በመሆኑም የቀረቡት ምሳሌዎች የቁጥር ስምምነት ችግር ብቻ ያለባቸው ሳይሆኑ የአረፍተ-ነገር ሰዋስው፣ የስርዓተ-ነጥቦች ችግር፣ የፊደል ግድፈትና ወዘተ. ችግር ያለባቸው ናቸው፡፡ ነገር ግን የተገለጹት ችግሮች በሚፈቅደው ቦታ ወደፊት ስለሚነሱ ከላይ የቀረበውን ንዑስ ርዕስ የሚመለከቱትን ብቻ እንመልከት።

በመሆኑም የመጀመሪያው አረፍተ-ነገር "አፈር ብዙ ጥቅም አላቸው" የሚለው የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ የቁጥር ስምምነት ችግር ይታይበታል፡፡ መሆን የነበረበት "አፈር ብዙ ጥቅም አለው---" በሚል ተስተካክሎ ቢፃፍ የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ ችግሮቹ ይቀረፍ ነበር፡፡ ሁለተኛው አረፍተ-ነገር ደግሞ ሰዎች ውሃ ለብዙ ነገር ይጠቀማል" የሚል ሲሆን ይህ አረፍተ-ነገር የስርዓተ-ነጥብ ችግር አለበት። ነገር ግን ለምሳሌ ከቀረበበት ርዕስ ጋር የሚገናኘው ችግር የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ የቁጥር አለመስማማት ነው። መሆን የነበረበትም "ሰዎች ውሃ ለብዙ ነገር ይጠቀማሉ። " በዚህ መንገድ ቢስተካከል ችግሮቹ ይቀረፉ ነበር፡፡

❖ "አፈር ብዙ ጥቅም አለው.።"

❖ "ሰዎች ውሃን ለብዙ ነገር ይጠቀማሉ."

❖ ጫት ጉዳት እንጅ ምንም ጥቅም የለውም"

## ለ. የመደብ አጠቃቀም ችግር

❖ "የሰወ ልጅ ሁለ ውሃ ባይኖር መኖር አልችልም።"

❖ "አፈር ለሰው ጠቃም ናት"

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎች አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው። በመሆኑም የቀረቡት ምሳሌዎች የመደብ አጠቃቀም ችግር ብቻ ያለባቸው ሳይሆኑ የአረፍተ-ነገር ሰዋስው፣ የስርዓተ-ነጥቦች ችግር፣ የፊደላት ግድፈት፣ የቁጥር ስምምነት ችግር፣ የቃል ድግግሞሽ እና ወዘተ. ችግር ያለባቸው ናቸው። ነገር ግን ከላይ የቀረበውን ንዑስ ርዕስ የሚመለከቱትን ብቻ እንመልከት።

በመሆኑም ከላይ በቀረቡት ምሳሌዎች ከላይ የተሰመረባቸው ቃላት የመደብ አመልካች ቅጥያዎችና የማሰሪያ አንቀጹ የተስማሙ አይደሉም። ቀጥለን አንዱን በምሳሌነት እንመልከት። የመጀመሪያው አረፍተ-ነገር "የሰወ ልጅ ሁሉ ውሃ ባይኖር መኖር

አይችልም።"የሚል ሲሆን አረፍተ-ነገሩ ቀደም ሲል ከላይ የጠቀስኳቸው ችግሮች በሙሉ ያለበት ነው፡፡ ስለዚህ የድርሰቱ ፀሐፊ መፃፍ የፈለገው ውሃ ባይኖር የሰው ልጅ ሁሉ መኖር አይችሉም። ለማለት ፈልጎ ነው፡፡ በአረፍተ-ነገሩ መጨረሻ ላይ የተሰመረበት የማሰሪያ አንቀጽ ቃል ደግሞ ሶስትኛ መደብ ብዙ ቁጥር አመልካች ነው። ስለዚህ ሁለቱም ተጣጥመው አይሄድም። ከዚህም የተነሳ የመደብ ቁጥር ስምምነት ችግር አለበት። በመሆኑም እንደሚከተለው ተስተካክለው ቢፃፉ የቃላት አጠቃቀምና ሰዋስዋዊ ስርዓቱን የጠበቁ አረፍተ- ነገሮች ስለሚሆኑ ተደራሲያንን ሊያግባቡ ይችላሉ።

- "የሰው ልጅ ሁሉ ውሃ ባይኖር መኖር አይችልም፡፡"
- "አፈር ለሰው ጠቃም ነው።"

### ሐ. የቃላት ቅደም ተከተል ችግር

የቃላት ቅደም ተከተል ችግር ማለት አንድ ቃል በተገቢው ቦታና የሚገባበትን የቦታ ቅደም ተከተል ሳይጠብቅ መጠቀም ማለት ነው።

- "ያለውሃ መኖር በጣም ይከብዳል ለሰው ልጅ።"
- "ጤንነታችንን ለመከታተል ሃክም ቤት መኖር አለበት በአካባቢያችን።"
- "የውሃ ጥቅም ተወርቶና ተናግሮ አያልቅም ብየ አስባለለሁ በበኩሌ።"

ከላይ የቀረቡ ምሳሌዎች አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በምሳሌነት የቀረቡ ናቸው። በመሆኑም ምሳሌዎቹ የተለያዩ የሰዋስው ችግር ያለባቸው ናቸው።ነገር ግን ከላይ የቀረበውን ንዑስ ርዕስ የሚመለከቱትን ብቻ እንመልከት።

የመጀመሪውን ምሳሌ ብናይ "ያለውሃ መኖር በጣም ይከብዳል ለሰው ልጅ።" የሚለው አገላለጽ ለንግግር ቢሆን ሊያግባባ ይችላል። ምክንያቱም የቋንቋ አቀባይና ተቀባይ አብረው መልዕክቱን ስለሚቀባበሉ ማስተካከያ በማድረግ መልዕክቱን መረዳት ይቻላል። ነገር ግን በጽህፈት ጊዜ መልክት አቀባዩና ተቀባዩ አብረው ስለማይገናኙና የቋንቋው ሰዋስው ስለማይፈቅድ በዚህ መልኩ መጠቀም ተገቢ አይደለም። ከዚህም በተጨማሪ መልዕክቱ በቀላል ለመልዕክት ተቀባዩ እንዳይተላለፍ እክል ይገጥመዋል። ስለዚህ ይህ አረፍተ-ነገር መፃፍ የሚገባው "ለሰው ልጅያለ ውሃ መኖር በጣም ይከብዳል፡፡" በሚል መቅረብ አለበት። ሁለተኛው ደግሞ "ጤንነታችንን ለመከታተል ሃክም ቤት መኖር አለበት በአካባቢያችን፡፡" የሚለው "ጤንነታችንን ለመከታተል በአካባቢያችን ሀክም ቤት መኖር አለበት።" በሚል ተስተካክሎ ቢፃፍ ሁሉንም ያግባባ ነበር። ሶስተኛው አረፍተ-

ነገር የስርዓተ-ነጥብ ችግር፣ የፊደላት ግድፈት፣ የቃላት ድረታና የመሳሰሉት ችግሮች ይታዩበታል። ሆኖም ከርዕሱ ጋር የሚሄደውን የቃላት ቅደም ተከተል ችግር ስናይ ባለቤቱ ማሰሪያ አንቀጽ ላይ ማሰሪያ አንቀጹ ደግሞ ባለቤት ላይ በመምጣቱ ተገቢውን ቅደም ተከተል አልጠበቀም። ስለዚህ "በበኩሌ የውሃ ጥቅም ተወርቶና ተናግሮ አያልቅም ብዬ አስባለሁ፡፡ "በሚል መልኩ ቢስተካከል የሰዋስው ስርዓቱን የተከተለ ይሆናል።

## 4.3. የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም

በዚህ ክፍል ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚታዩ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች በመቁጠር የሚከተለው መረጃ ተተንትኗል።

ሰንጠረዥ 6 የተጠኝዎች የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም በተመለከተ ከድርሰቶቻቸው የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| የስህተት አነይት | አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች | | | | | | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቃላት አጠቃቀም | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | የቃላት አጠቃቀም | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | የቃላት አጠቃቀም | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | የቃላት አጠቃቀም | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | የቃላት አጠቃቀም |
| | 15 | 2625 | 175 | 193 | 12.86 | 10.34% | 22 | 2835 | 108.86 | 207 | 9.4 | 7.2% |

ከላይ በቀረበው ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ 193 የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ሲቆጠሩ አማርኛ ኢ-አፊ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ደግሞ 207 ስህተቶች ተቆጥረዋል። በመቀጠል የስህተቱን መጠን በመቶኛ ለማወቅ ከዚህ በፊት የተሰራበትን ቀመር ተግባራዊ በማድረግ ለማስላት ተሞክሯል። በዚሁም መሠረት አማርኛ አፊ ፈት ተማሪዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የፈጸሙት አማካይ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተትን ማወቅ ስለሚያስፈልግ በስህተትነት የተመዘገቡትን ከድርሰት ቁጥር ጋር በማካፈል አማካይ የስህተት መጠኑን ለማወቅ ተችሏል፡በዚህም መሠረት 193 ለ15 ስናካፍለው 12.86 አማካይ ስህተት እናገኛለን። ተማሪዎቹ ድርሰት የፃፉባቸው አማካይ ቃላት ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለፀው 175 መሆኑ ይታወቃል፡በመቀጠሌ የተፈጸመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ እንደሚከተለው ተሰልቷል።

<u>አማካይ ስህተት</u> × 100 |<u>12.86</u> X 100 = 7.34%|

አማካይ ቃላት 175

በሌላ በኩል አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚገኘውን ስህተት በመቶኛ ለማወቅ ከ|አይ በቀረበው መልኩ ተሰልቷል፡፡ በመሆኑም ተማሪዎቹ በፃፊት ድርሰት ውስጥ 207 የሚሆኑ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ስህተቶች ተቆጥረው ተመዝግበዋል። የስህተቱን አማካይ ለማወቅ ደግሞ በስህተትነት የተመዘገቡትን ለድርሰቱ ቁጥር በማካፍል ማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት 207 ሲካፈል ለ22 9.4 አማከይ ስህተት መሆኑ ተረጋግጧል። ድርሰት የፃፉበት አማካይ ቃላት ቀደም ሲል እንደተገለፀው 106.75 ነው። በመቀጠል የተፈፀመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ለማወቅ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

<u>አማካይ ስህተት</u> × 100 |<u>9.4</u> X 100 = 7.2%|

አማካይ ቃላት 108.86

ከላይ ካሉት የመረጃ ውጤቶች መገንዘብ እንደተቻለው አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች ከአፍ ፊት ተማሪዎች በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው የተሻሉ እንደሆነ ያስመዝገቡት ስህተት ያመለክታል። ምክንያቱም አማርኛ አፍ ፊት ተማሪዎች 10.34% የስርዓተ-ነጥብ ስህተቶችን ሲያስመዘግቡ አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች ደግሞ 7.2% የስርዓተ-ነጥብ ስህተቶችን በማስመዝገባቸው በጥናቱ ውጤት መሠረት አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን ያመለክተናለ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ተማሪዎች በፃፉት ድረሰት ውስጥ የሚታየውን ሰዋስዋዊ ስህተት ከፆታ አንፃር እንመልከት።

ሰንጠረዥ 7. ተጠኝ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀምን በተመለከተ በጽሁፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛበ/ፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | መቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍ ፊት | አማርኛ አፍ ፊት | አማርኛ ኢ-አፍ ፊት | አማርኛ ኢ-አፍ ፊት |
| የትምህርት ክፍል መምህራን ስለአማርኛ ስርዓተ-ነጥቦችና አጠቃቀም አስተምረውኛል | ፈጽሞ አልስማማም | 0 | 0% | 0 | 0% |
| | አልስማማም | 0 | 0% | 1 | 4.54% |
| | እስማማለሁ | 3 | 20% | 10 | 45.45% |
| | በጣም እስማማለሁ | 12 | 80% | 11 | 50% |

ከላይ ከቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍ ፊት ተማሪዎች 100% መምህራን በጽህፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ስለ አማርኛ ስርዓተ-ነጥቦችና አጠቃቀም እንደሚያስተምሯቸው በሰጡት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ለማረጋገጥ ተችሏል።

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች ውስጥ 95% የሚሆኑት መምህራን በጽህፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ስለ አማርኛ ስርዓተ-ነጥቦችና አጠቃቀም እንደሚያስተምሯቸው የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 4.54% የሚሆኑት ደግሞ መምህራን በጽህፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ስለ አማርኛ ስርዓተ-ነጥቦችና አጠቃቀም እንደማያስተምሯቸው የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡ ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍ ፊትም ሆኑ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች አብዛኞቹ እንደገለጹት መምህራን በጽሕፈት ትምህርት ክፍለ ጊዜ ስለ አማርኛ ስርዓተ-ነጥቦችና አጠቃቀም እንደሚያስተምሯቸው ነው።

ነገር ግን ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እና በተግባር በድርሰቶቻቸው የታየው ተመሳሳይ ነው ለማለት ያስቸግራል። ምክንያቱም አማርኛ አፍ ፊትም ይሁን ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በፃፉት ድርሰት ላይ የታየው የስርዓተ-ነጥብ ችግር የአማርኛ ስርዓተ-ነጥቦችን አያውቁም የሚያስብል ነው።

በመሆኑም የሰጡት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ መምህራንን ከመፍራት አኳያ የመለሱት መሆንን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ከዚህ አንፃር የተሰጠው ምላሽ ከድርሰቶቻቸው ጋር ተያኻነት ያለውና ተገቢ ነው ማለት አይቻልም። ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ አማርኛ አፍ ፊትና ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀም ችግሮች ከሚገኙባቸው አረፍተ-ነገሮች ለአብነት ያህል በማሰረጃነት ለማቅረብ ተሞክሯል። በአረፍተ- ነገሮቹ ውስጥ ጎላ ብለው ከሚስተዋሉ ስህተቶች አንፃር በመመልከት እንጂ በእያንዳንዱ አረፍተ-ነገር ውስጥ የሚታየው ስህተት አንድ ብቻ አይደለም።

ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቃም ችግሮች

## 1. አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቃም ችግሮች

### ሀ. የአራት ነጥብ አጠቃቀም ችግሮች

- "---ህይውት ላላቸው ሁሉ ውሃ ያስፍልጋል__"
- "ጫት መቃም ጉዳት አለው__"
- "ውሃ ለምጠጥና ለመታጠብ ያገለግላል__"
- "የስራ ግዚያቸውን በጫት ያሳለፋሉ__"

ከላይ በምሳሌዎች የቀረቡት አረፍተ-ነገሮች አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች የተወሰደ ሲሆን ያለባቸውን ሰዋስዋዊ ችግሮች ትተን ሁሉም በአረፍተ-ነገራቸው መጨረሻ ላይ አራት ነጥብ አልተጠቀሙም። ይህም የሚያሳየው ተማሪዎቹ የስረዓተ-ነጥቦችን ጥቅም ካለመረዳትና አጠቃቀማቸውንም ካለማወቅ የመነጨ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ይጠቁመናል።

### ለ. የሁለት ነጥብ፣ ነጠላ ሰረዝና ትምህርተ-ጥቅስ አጠቃቀም ችግሮች

- " --- ጫትመቃም ጉዳት አለው"
- " --- ኤች አይ ቪ ኤድስ ዘር ፆታ ሃይማኖት የትምህርት ደረጃ አይለይም"
- " --- ኤድስ ለመጀመሪያ ግዘ የተገነው አመሪካ ነው ተብሎ ይነገራል"

ከላይ የቀረቡት ምሳሌዎች በንዑስ ርዕሱ እንደተጠቀሰው የሁለት ነጥብ፣ ነጠላ ሰረዝና ትምህርተ-ጥቅስ አጠቃቀም ችግሮች የሚታዩባቸው አረፍተ-ነገሮች ናቸው። በመሆኑም የመጀመሪያውና ሁለተኛው አረፍተ-ነገሮች የሁለት ነጥብ አጠቃቀም ችግር ያለባቸው ናቸው። በኮምፒውተር ጽህፈት ጊዜ ለሁለት ነጥብ ቦታ እየተው መፃፍ ይቻላል። በእጅም ጽህፈት ቢሆን እንዱሁ ማድረግ ይቻላል። ነገር ግን በዚህ መንገድ መጠቀም አረፍተ-ነገሮቹን አንብቦ ለመረዳት በጣም ያስቸግራል።

ሌላው ደግሞ ሦስተኛው አረፍተ-ነገር ዝርዝር ነገሮችን የያዘ ሲሆን ነጠላ ሰረዝ መጠቀም ሲኖርባቸው አልተጠቀሙም። አራተኛውና አምስተኛው አረፍተ-ነገሮች በድርሰታቸው ላይ የጻፉት የሰውን ሀሳብ ወይም ንግግር በመሆኑ በጥቅስ ምልክት መቀመጥ ነበረባቸው። ነገር ግን ድርሰቱን የጻፉት ከሊላይ በምሳሌው እንደተቀመጠው ነው፡፡ ከአንድ እስከ ሶስት ያሉትን አጥኝው በጥቅስ ምልክት ያስቀመጠው በምሳሌነት

የተወሰደ የሌሎች ሀሳብ በመሆኑ ነው። ሆኖም የመጨረሻው በጥቅስ ምልክት ውስጥ ያልገባው በቀረበበት መንገድ እንዳለ ለማሳየት ታስቦ ነው፡፡ በመሆኑም ሁሉም እንደሚከተለው ተስተካክለው መፃፍ ነበረባቸው።

- " --- ጫት መቃም ጉዳት አለው።"
- " --- ኤች አይ ቪ ኤድስ ዘር፣ ፆታ፣ ሃይማኖት፣ የትምህርት ደረጃ ወዘተ አይለይም።
- " --- "ኤድስ ለመጀመሪያ ግዜ የተገኘው አሜሪካ ነው" ተብሎ ይነገራል።

**2. ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቃም ችግሮች**

**ሀ. የአራት ነጥብ አጠቃቀም ችግሮች**

- "አፈር ቡዙ ጥቅም አለው_____ "
- "የኤድስ መከላከያ መንገድይታወቃል_____"
- "አፈርን በሁለት ዓይነት መልኩ ማየት እንችላለን_____ "
- "ያለዉሃ መኖር በጣም ይከብዳል፟___ "

ከላይ በምሳሌዎች የቀረቡት አረፍተ-ነገሮች አማርኛ ኢ-አፈ ፊት ተማሪዎች ከፃፏቸው ድርሰቶች የተወሰደ ሲሆን ያለባቸውን ሰዋስዋዊ ችግሮች ትተን ሁሉም በአረፍተ-ነገራቸው መጨረሻ ላይ አራት ነጥብ አልተጠቀሙም። ይህም የሚያሳየው ተማሪዎቹ የስረዓተ-ነጥቦችን ጥቅም ካለመረዳትና አጠቃቀማቸውንም ካለማወቅ የመነጨ እንደሆነ የጥናቱ ውጤት ይጠቁመናል፡፡ ነገር ግን ከአማርኛ አፈ ፊት ተማሪዎች አንፃር ሲነፃፀሩ አማርኛ አፈ ፊት ተማሪዎች አልፎ አልፎ ካልሆነ በቀር ሁለም በፃፏቸው ድርሰቶች ላይ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀማቸው በጣም የተሻለ ነው። ስለዚህ የስርዓተ-ነጥቦችን አጠቃቀም ያውቃሉ ማለት ያስችላል።

**ለ. የሁለት ነጥብ፣ ነጠላ ሰረዝና ትምህርተ-ጥቅስ አጠቃቀም ችግሮች**

- "---መንገድይታወቃል
- "ከፊተኛድርሻ
- የአፈር ጥቅምቡዙ ነው

ከላይ የቀረቡት ምሳሌዎች በንዑስ ርዕሱ እንድተጠቀሰው የሁለት ነጥብና ትምህርተ-ጥቅስአጠቃቀም ችግሮች የሚታዩባቸው አረፍተ-ነገሮች ናቸው። በመሆኑም

የመጀመሪያው አረፍተ- ነገር የሁለት ነጥብና የአራት ነጥብ አጠቃቀም ችግር ያለበት ነው፡፡ በኮምፒውተር ጽህፈት ጊዜ ለሁለት ነጥብ ቦታ እየተው መፃፍ ይቻላል። በእጅም ጽህፈት ቢሆን እንዲሁ ማድረግ ይቻላል። ነገር ግን በዚህ መንገድ መጠቀም አረፍተ-ነገሩን አንብቦ ለመረዳት በጣም ያስቸግራል፡፡ ሁለተኛውና ሶስተኛው አረፍተ-ነገሮች በድርሰታቸው ላይ የጻፉት የሰውን ሀሳብ ወይም ንግግር በመሆኑ በጥቅስ ምልክት መቀመጥ ነበረባቸው። ነገር ግን ድርሰቱን የጻፉት ከላይ በምሳሌው እንደተቀመጠው ነው፡፡ የመጀመሪያውን አአረፍተ-ነገር አጥኚው በጥቅስ ምልክት ያስቀመጠው በምሳሌነት የተወሰደ የሌሎች ሀሳብ በመሆኑ ነው። ሆኖም የመጨረሻዎቹ ሁለቱ በጥቅስ ምልክት ውስጥ ያልገቡት በቀረበበት መንገድ እንዳለ ለማሳየት ታስቦ ነው። በመሆኑም ሁሉም እንደሚከተለው ተስተካክለው መፃፍ ነበረባቸው።

- "---መንገድ ይታወቃል።
- "ከፊተኛ ድርሻ
- የአፈር ጥቅም ቡዙ ነው።

## 4.4. የአንቀጽ አደረጃጀት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ያለውን የአንቀጽ አንድነት፣ የአረፍተ-ነገር ተያዥነትና ዝምድና፣ የአያያዥ ቃላት አጠቃቀምን በተመለከተ የተገኘውን ጥናታዊ ውጤት ቀጥሎ በቀረበው መልኩ ለመተንተን ተሞክሯል።

ሰንጠረዥ8. የተጠኚ ተማሪዎች የአንቀጽ አደረጃጀትን በተመለከተ ከድርሰቶቻቸው የተገኘውን ውጤት የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| የስህተት አነይት | አማርኛ አፍ ፊት ተማሪዎች | | | | | | አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቃላት አጠቃቀም | የድር ሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | የቃላት አጠቃ ቀም | የድርሰ ቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | የቃላት አጠቃ ቀም | የድር ሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | የቃላት አጠቃ ቀም | የድርሰ ቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | የቃላት አጠቃ ቀም |
| | 11 | 1,925 | 175 | 39 | 5.54 | 2.03% | 20 | 2,135 | 106.75 | 88 | 4.4 | 4.12% |
| | 15 | 2625 | 175 | 37 | 2.46 | 1.4% | 22 | 2835 | 128. 86 | 86 | 3.9 | 3% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት መረዳት እንdሚቻለው አማርኛ አፊ ፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ 37 የአንቀጽ አደረጃጀት ስህተቶች ሲቆጠሩ አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ደግሞ 86 ስህተቶች ተቆጥረዋል። በመቀጠል የስህተቱን መጠን በመቶኛ ለማወቅ ከዚህ ቀደም ሲል የተሰራበትን ቀመር

ተግባራዊ በማድረግ ለማስላት ተሞክሯል። በዚሁም መሠረት አማርኛ አፊ ፊት ተማሪዎች በድርሰቶቻቸው ውስጥ የፈጸሙት አማካይ የአንቀጽ አደረጃጀት ስህተትን ማወቅ ስለሚያስፈልግ በስህተትነት የተመዘገቡትን ከድርሰት ቁጥር ጋር በማካፈል አማካይ የስህተት መጠኑን ለማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት 37 ለ15 ስናካፍለው 2.46 አማካይ ስህተት እናገኛለን፡፡ ተማሪዎቹ ድርሰት የፃፈባቸው አማካይ ቃላት ደግሞ ቀደም ሲል እንደተገለፀው 175 መሆኑ ይታወቃል፡፡ በመቀጠል የተፈጸመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ እንደሚከተለው ተሰልቷል።

<u>አማካይ ስህተት</u> × 100 |<u>2.46</u> X 100 = 1.4%|

አማካይ ቃላት 175

በሌላ በኩል አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የሚገኘውን ስህተት በመቶኛ ለማወቅ ከላይ በተሰራው መልኩ ተሰልቷል። በመሆኑም ተማሪዎቹ በፃፉት ድርሰት ውስጥ 86 የሚሆኑ የአንቀጽ አደረጃጀት ስህተቶች ተቆጥረው ተመዝግበዋል። የስህተቱን አማካይ ለማወቅ ደግሞ በስህተትነት የተመዘገቡትን ለድርሰቱ ቁጥር በማካፈል ማወቅ ተችሏል። በዚህም መሠረት 86 ለ22 ሲካፈል 3.9 አማከይ ስህተት መሆኑ ተረጋግጧል። ድርሰት የፃፉበት አማካይ ቃላት ቀደም ሲል እንደተገለፀው 128. 86 ነው፡፡ በመቀጠል የተፈፀመው ስህተት በመቶኛ ምን ያህለ እንደሆነ ለማወቅ እንደሚከተለው ተሰልቷል፡፡

<u>አማካይ ስህተት</u> × 100 |<u>3.9</u> X 100 = 4.12%|

አማካይ ቃላት 28.86

ከላይ ካሉት የመረጃ ውጤቶች መገንዘብ እንደተቻለው አማርኛ አፍ ፊት ተማሪዎች ከኢ-አፊ ፊት ተማሪዎች በአንቀጽ አደረጃጀት ችሎታቸው የተሻሉ እንደሆነ ያስመዝገቡት የስህተት መጠን ያመለክታል፡፡ ምክንያቱም አማርኛ አፊ ፊት ተማሪዎች 2.03% የአንቀጽ አደረጃጀት ስህተቶችን ሲያስመዘግቡ አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች ደግሞ 4.12% የአንቀጽ አደረጃጀት ስህተቶችን በማስመዝገባቸው በጥናቱ ውጤት መሠረት አማርኛ አፍ ፊት ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸው ተረጋግጧል፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ተማሪዎች በፃፉት ድረሰት ውስጥ የሚታየውን የአንቀጽ አደረጃጀት ስህተቶች ከዖታ አንፃር እንመልከት።

ሰንጠረዥ9. ተጠኝ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የአንቀጽ አደረጃጀትን በሚመለከት በጽሑፍ መጠይቅ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛበ/ፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | መቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍ ፈት | አማርኛ አፍ ፈት | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት |
| ድርሰት ስጽፍ የአንቀጽ አንነት፣ ተያያዥነት፣ ዝምናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቄ እጽፈለሁ | ፈጽሞ አልስማማም | 3 | 20% | 2 | 9% |
| | አልስማማም | 3 | 20% | 3 | 14% |
| | እስማማለሁ | 6 | 40% | 17 | 68.18% |
| | በጣም እስማማለሁ | 3 | 20% | 0 | 0% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ አፈ ፈት ተማሪዎች ውስጥ 60% የሚሆኑት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፈ የአንቀጽ አንድነት፣ ተያያዥነት፣ ዝምድናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቀው እንደሚጽፈ የገለጹ ሲሆን 40% የሚሆኑት አማርኛ አፈ ፈት ተማሪዎች ደግሞ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፍ የአንቀጽ አንድነት፣ ተያያዥነት፣ ዝምድናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቀው እንደማይጽፉ የሰጡት መረጃ ያመለክታል።

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፈ ፈፍፃት ተማሪዎች ውስጥ 68% የሚሆኑት በጽህፃት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ የአንቀጽ አንድነት፣ ተያያዥነት፣ ዝምድናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቀው እንደሚጽፉ የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 23% የሚሆኑት ደግሞ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ የአንቀጽ አንድነት፣ ተያያዥነት፣ ዝምድናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቀው እንደማይጽፉ የተገኘው መረጃ ያሳያል።።ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍ ፈትም ሆኑ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች አብዛኞቹ እንደገለጹት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲጽፉ የአንቀጽ አንድነት፣ ዝምድናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቀው እንደማይጽፉ የተገኘው መረጃ ያሳያል።

ነገር ግን ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እና በተግባር በድርሰቶቻቸው የታየውን ተመሳሳይነት አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ከላይ በሰንጠረዥ 14 የሰጡት መረጃ ከኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች አንፃር ተዓማኒነት አለው ለማለት ያስችላል። ምክንያቱም አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ከኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የተሻለ የአንቀጽ አንድነት፣ ተያያዥነት፣

ዝምድናና የአያያዥ ቃላትን ጠብቀው በመፃፍ የተሻለ መሆናቸውን ከጥናቱ መረዳት ይቻላል። ሆኖም አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ በዘፈቀደ ወይም መምህራንን ከመፍራት የመነጨ እንደሆነ መገመት ይቻላል።

## 4.5. በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የታዩ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም

አማርኛ ቋንቋ አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩትን የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም ስህተቶችን በመቁጠር ከዚህ በታች በቀረበው መሠረት ትንተና ተሰጥቷል።

ሰንጠረዥ10. የተጠኝ ተማሪዎች በፃፉት ድርሰት ውስጥ የታዩ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም በተመለከተ የሚያሳይ መረጃ

| የስህተት አነይት | አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች | | | | | | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የቃላት አጠቃቀም | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | የቃላት አጠቃቀም | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | የቃላት አጠቃቀም | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | የቃላት አጠቃቀም | የድርሰቶቹ ብዛት | የቃላት ብዛት | የቃላት አጠቃቀም |
| | 11 | 1,925 | 175 | 226 | 20.54 | 17.74% | 20 | 2,135 | 106.75 | 861 | 43.05 | 40.33 % |
| | 15 | 2625 | 175 | 224 | 14.93 | 10,24% | 22 | 2835 | 128. 86 | 860 | 39 | 30% |

ከሰንጠረዥ15. መመልከት እንደሚቻለው በፃፉት ድርሰት ውስጥ የታዩ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀምን በተመለከተ አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው 15 ድርሰቶች 2625 ቃላትን የተጠቀሙ ሲሆን በድርሰቶቹ ውስጥ 224 ፊደላት በስህተትነት ተቆጥረው ተመዝግበዋል። እንዲሁም አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው 22 ድርሰቶች 2835 ቃላትን የተጠቀሙ ሲሆን በዴርሰቶቹ ውስጥ 861 ፍደላት በስህተትነት ተቆጥረው ተመዝግበዋል፡፡ ከዚህ አንፃር አማርኛ ቋንቋ አፍ ፈት ተማሪዎች የተመዘገበባቸው ስህተት መጠን አማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍ ፈት ከሆኑት ተማሪዎች ያነሰ ስለሆነ የተሻለ የፊደላት አጠቃቀም ችሎታ አላቸው ማለት ይቻላል። እንዲሁም በተፃፉት ድርሰቶች ውስጥ የተፈጸመውን አማካይ የፊደላት ስህተት ለማወቅ የተቆጠረውን የፊደላት ስህተት ብዛት ከድርሰቶቹ ቁጥር ጋር በማካፈል ማወቅ ተችሏል፡፡ በዚህም መሠረት አማርኛ አፈ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ያሉትን 226 የፊደላት ስህተቶች ለጠቅላላ ድርሰቶቹ (ለ15 ድርሰቶች) ስናካፍለው የአንድ ተማሪ ድርሰት በአማካኝ በ14.93 ፊደላት ስህተት የተፃፈ መሆኑን ማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም አማካይ

ስህተቱን ለአማካይ ቃላት በማካፈልና በ100 በማብዛት የተመዘገበውን ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ተችሏል።

<u>አማካይ ስህተት</u> × 100 | <u>14.93</u> X 100 = 10,24% |

አማካይ ቃላት 175

በተጨማሪም ከሰንጠረዥ 15. መመልከት እንደሚቻለው በፃፉት ድርሰት ውስጥ የታየ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀምን በተመለከተ አማርኛ ኢ-አፊ ፊት ተማሪዎች በፃፏቸው 20 ድርሰቶች 2835 ቃላትን የተጠቀሙ ሲሆን በድርሰቶቹ ውስጥ 860 ፊደላት በስህተትነት ተቆጥረው ተመዝግበዋል። እንዲሁም በተፃፉት ድርሰቶ ውስጥ የተፈጸመውን አማካይ የፊደላት ስህተት ለማወቅ የተቆጠረውን የፊደላት ስህተት ብዛት ከድርሰቶቹ ቁጥር ጋር በማካፈል ማወቅ ተችሏል።

በዚህም መሠረት አማርኛ አፊ ፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ ያለትን 860 የፊደላት ስህተቶች ለጠቅላላ ድርሰቶቹ (ለ22 ደርሰቶች) ስናካፍለው የአንድ ተማሪ ድርሰት በአማካኝ በ39 ፊደላት ስህተት የተፃፈ መሆኑን ማወቅ ተችሏል። በተጨማሪም አማካይ ስህተቱን ለአማካይ ቃላት በማካፈልና በ100 በማብዛት የተመዘገበውን ስህተት በመቶኛ ምን ያህል እንደሆነ ማወቅ ተችሏል።

<u>አማካይ ስህተት</u> × 100 | 39 X 100 = 30% |

አማካይ ቃላት 128.86

ከላይ የተገኘው ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍ ፊትና ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የተመዘገቡት የፊደላት ስህተቶች ሲነፃፀሩ አማርኛ አፍ ፊት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ 10,24% ያህል የፊደላት አጠቃቀም ስህተት እንዳለባቸውና አማርኛ ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች ደግሞ 10,24% ያህል ስህተት እንዳለባቸው የተገኘው ውጤት ያሳያል። ከዚህም አንፃር አማርኛ አፍ ፊት ተማሪዎች አነስተኛ ስህተት ስለተገኘባቸው በፊደላት አጠቃቀም ችሎታ የተሻሉ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡ በሌላ በኩል የፊደላት አጠቃቀም ችሎታ ከፆታ አንፃር ስንመለከት እንደሚከተለው ይሆናል።

ሰንጠረዥ11. የተጠኝ ተማሪዎች የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም ችሎታን በተመለከተ ለቀረበላቸው ጥያቄ የሰጡት ምላሽ የሚያሳይ መረጃ

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ/በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | መቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍ ፈት | አማርኛ አፍ ፈት | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት |
| የምጽፈው ድርሰት ትክክለኛ የፊደል አጣጣል ይዞ የሚጓዝ ነው | ፈጽሞ አልስማማም | 1 1 | 9.09% 6% | 0 0 | 0% 0% |
| | አልስማማም | 2 3 | 18.18% 20% | 1 2 | 5% 9.09% |
| | እስማማለሁ | 4 5 | 36.36% 33.33% | 17 16 | 75% 72.72% |
| | በጣም እስማማለሁ | 4 6 | 36.36% 40% | 2 4 | 10% 18.18% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ውስጥ 73.33% የሚሆኑት ድርሰት ሲጽፉ ትክክለኛውን የፊደላት ቅርጽ እንደሚጠቀሙ 26% የሚሆኑት አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ደግሞ ድርሰት ሲጽፉ ትክክለኛውን የፊደላት ቅርጽ እንደማይጠቀሙ በሰጡት የጽሑፍ መጠይቅ ምላሽ ማረጋገጥ ተችሏል።

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ውስጥ 90% የሚሆኑት ድርሰት ሲጽፉ ትክክለኛውን የፊደላት ቅርጽ እንደሚጠቀሙ የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 9.09%% የሚሆኑት ደግሞ ድርሰት ሲጽፉ ትክክለኛውን የፊደላት ቅርጽ እንደማይጠቀሙ የተገኘው መረጃ ያሳያል።

ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፈ ፈትም ሆኑ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች አብዛኞቹ እንደገለጹት ድርሰት ሲጽፉ ትክክለኛውን የፊደላት ቅርጽ እንደሚጠቀሙ ጥናቱ ያሳየናል፡፡

ነገር ግን ተማሪዎች የሰጡት ምላሽ እና በተግባር በድርሰቶቻቸው የታየው ተመሳሳይ ነው ለማለት ያስቸግራል፡፡ ምክንያቱም አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ከላይ በሰንጠረዥ 15 በቀረበው የድርሰታቸው መረጃ ውጤት መሠረት 10,24% የሚሆን የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም ስህተት ሲታይባቸው አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ደግሞ በፃፉት ድርሰት 40.33% የሚሆኑ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም ስህተት ታይቶባቸዋል።

በመሆኑም የሰጡት የጽሐፍ መጠይቅ ምላሽ የሚጽፉት የፊደላትት ቅርጽ ትክክል ነው ብለው ስለሚያስቡ ነው፡፡ ስህተታቸውንም እንዲያውቁ የመምህራን ሚና ከፍተኛ ነው፡፡

በመሆኑም መምህራን ተማሪዎች ተግባራዊ ልምምድ እንዲያደርጉ በማድረግ ማስተካከያ እንዲያደርጉ ድጋፍ ሊያደርጉላቸው ይገባል። ከዚህ አንፃር የተሰጠው ምላሽ ከድርሰቶቻቸው ጋር ተያኸነት ያለውና ተገቢ ነው ማለት አይቻልም።

ስለዚህ ከዚህ ቀጥሎ ደግሞ አማርኛ አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የፊደላት አጠቃቀም ችግሮች ከሚገኙባቸው አረፍተ-ነገሮች ለአብነት ያህል በማሰረጃነት ለማቅረብ ተሞክሯል። በአረፍተ- ነገሮቹ ውስጥ ጎላ ብለው ከሚስተዋሉ ስህተቶች አንፃር በመመልከት እንጂ በእያንዳንዱ አረፍተ-ነገር ውስጥ የሚታየው ስህተት አንድ ብቻ አይደለም።

## ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የፊደላት ስህተቶች

### 1. አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የፊደላት ስህተቶች

"ከምባሉት፣ አደሰ፣ የምያጋልጥ፣ ያአስፈልጋለ፣ ጥንነታቸው ሁለ እና ወዘተ..."

ከላይ በምሳሌነት የቀረቡት ቃላት አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች በፀፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በተገኙ ቃላት የታዩ የፊደላት ግድፈቶች ናቸው። እነዚህም ግድፈቶች ወይም ስህተቶች የተፈጠሩት ተማሪዎቹ ፊደላትንና አጠቃቀማቸውን በአግባቡ ለይቶ ካለማዎቅ የመጣ መሆኑን ከስህተቶቹ ማወቅ ይቻላል፡፡ በምሳሌዎቹ ከቀረቡት ውስጥ ከሁለቱ ቃላት ማለትም "አብዛህኛውን" እና "ለበልጋ መስሪያ" ከሚሉት ቃላት በስተቀር ሌሎቹ በሙሉ ፊደላትንና አጠቃቀማቸውን በአግባቡ ለይቶ ካለማወቅ የመጣ ችግር ነው። "አብዛህኛውን" እና "ለበልጋ መስሪያ" የሚሉት ቃላት ግን ከዘዬ ወይም ከቀበሌኛ ቋንቋ አጠቃቀም ተጽዕኖ የመጣ መሆኑ ግለጽ ነው። በመሆኑም በምሳሌነት የቀረቡትን ቃላት ከፃፉት ድርሰት አውድ አንፃር ምን ለማለት ፈልገው እንድህ እንደፃፉ ከዚህ በታች በፃፉት ቃላት ቅንፍ ውስጥ ተቀምጧል። "ከምባሉት (ከምባሉት)፣ አደሰ፣ (አደሰ)፣ የምያጋልጥ (የምያጋልጥ)፣ ያአስፈልጋለ (ያአስፈልጋል)፣ ሁለ (ሁለ) እና ወዘተ..."

### 2. ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በፃፏቸው ድርሰቶች ውስጥ የታዩ የፊደላት ስህተቶች

- "ለጀ፣ ለመሸሽእል፣ እየጠቃ፣ ለመጽዳት፣ መቀም፣ አቻይቪ፣ ፍጥረተት፣ ጠቃም፣ ለእርሽ፣ የምቅሙ ያስጥብቃል"

ከላይ በምሳሌነት የቀረቡት ቃላት አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በፀፏቸው ድርሰቶች ውስጥ በተገኙ ቃላት የታዩ የፊደላት ግድፈቶች ናቸው። እነዚህም ግድፈቶች ወይም ስተቶች የተፈጠሩት ተማሪዎቹ ፊደላትንና አጠቃቀማቸውን በአግባቡ ለይቶ ካለማወቅ

የመጣ ብቻ አለመሆኑን ከስህተቶቹ ማዎቅ ይቻላል፡፡ ይህም ችግር ሊፈጠር የቻለው በአፍ መፍቻ ቋንቋ ተጽዕኖ ምክንያት የመጣ ችግር መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ በመሆኑም በምሳሌነት የቀረቡትን ቃላት ከፃፉት ድርሰት አውድ አንፃር ምን ለማለት ፈልገው እንዲህ እንደፃፉ ከዚህ በታች በፃፉት ቃላት ቅንፍ ውስጥ ተቀምጧል።

- "ለጀ (ልጅ)፣ ለመሽሽእል (ለማሻሻል)፣ እየጠቃ (እያጠቃ)፣ ለመጽዳት (ለማጽዳት)፣ መቀም (መቃም)፣ አቻይቪ (ኤች አይቪ)፣ ፍጥረተት (ፍጥረታት)፣ ጠቃም (ጠቃሚ)፣ ለእርሽ (ለእርሻ)፣ የምቅሙ (የሚቅሙ)፣

## 4.6. ተማሪዎች ለጽሕፈት ችሎታ ያላቸው ፍላጎት

ተማሪዎች የጽህፈት ችሎታን ለማዳበር ከሚያስችሏቸው ነገሮች ውስጥ የመጀመሪያው ለጽህፈት ትምህርት ያሏቸው ፍላጎት ነው። በመሆኑም ለጽህፈት ትምህርት ያላቸውን ፍላጎት ለማወቅ ያስችላል ተብለው በጽሁፍ መጠይቁ ውስጥ ለተዘረዘሩት ጥያቄዎች የሰጡትን ምላሽ እንደሚከተለው ለማቅረብ ተችሏል።

ሰንጠረዥ12. ተጠኝ ተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት እንዳላቸውና እንደሌላቸው ከማወቅ ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ/በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | መቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍ ፈት | አማርኛ አፍ ፈት | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት |
| የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት አለኝ | ፈጽሞ አልስማማም | 0 | 0% | 2 | 9.09% |
| | አልስማማም | 1 | 6.66% | 1 | 4.54% |
| | እስማማለሁ | 9 | 60% | 11 | 50% |
| | በጣም እስማማለሁ | 5 | 33.33% | 8 | 36.36% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ አፊ ፈት ተማሪዎች ውስጥ 93.33% የሚሆኑት የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት እንዳላቸው የገለጹ ሲሆን 6.66% የሚሆኑት አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ደግሞ የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት እንሌላቸው የሰጡት መረጃ ያመለክታል።

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፊ ፈት ተማሪዎች ውስጥ 86.36% የሚሆኑት የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት እንዳላቸው የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 13.33% የሚሆኑት ደግሞ የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት እንሌላቸው የተገኘው የጥናት ውጤት

ያሳያል። ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍ ፈትም ሆኑ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች አብዛኞቹ እንደገለጹት የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት እንዳላቸው መግለፃቸውን ከጥናቱ ለማረጋገጥ ተችሏል።

## 4.7. መምህራን ለጽሕፈት ትምህርት የሚሰጡት ትኩረት

ተማሪዎች ድርሰት ለመፃፍ የተሻለ ችሎታ እንዲኖራቸው በግላቸው ከሚያደርጉት ጥረት በተጨማሪ መምህራኖቻቸው ድጋፍ ሊያደርጉላቸው ይገባል። በመሆኑም መምህራን ተማሪዎቹን ይድግፉ እንደሆን ለቀረበላቸው የጽሐፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ከዚህ ቀጥሎ ለማቅረብ ተሞክሯል።

ሰንጠረዥ13. ተጠኝ ተማሪዎች መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጣሉ ተብለው ለቀረበላቸው የጽሐፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ/በፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | መቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍ ፈት | አማርኛ አፍ ፈት | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት |
| መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጣሉ | ፈጽሞ አልስማማም | 3 | 20% | 4 | 18.18% |
| | አልስማማም | 6 | 40% | 4 | 18.18% |
| | እስማማለሁ | 5 | 33.33% | 7 | 31.81% |
| | በጣም እስማማለሁ | 1 | 6% | 7 | 31.81% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት አንደሚቻለው ከአማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ውስጥ 60% የሚሆኑት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ስትጽፉ መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጧችኋል? ተብለው ለቀረበላቸው የጽሐፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ማስተካከያና ግብረ-መልስ እንደማይሰጧቸው የገለጹ ሲሆን 39.33% የሚሆኑት አማርኛ አፍፈት ተማሪዎች ደግሞ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ስትጽፉ መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጧችኋል? ተብለው ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ ማስተካከያና ምግበ ምላሽ እንደሚሰጧቸው የሰጡት መረጃ ያመለክታል።

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ውስጥ 63.62% የሚሆኑት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ስትጽፉ መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ

የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጧችኋል? ተብለው ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ ማስተካከያና ምግበ ምላሽ እንደሚሰጧቸው የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 40% የሚሆኑት በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ስትጽፉ መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጧችኋል? ተብለው ለቀረበላቸው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ ማስተካከያና ምግበ ምላሽ እንደማይሰጧቸው የተገኘው መረጃ ያሳያል። ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍ ፈትም ሆኑ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች አብዛኞቹ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ ድርሰት ሲትጽፉ መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካከያና ምግበ ምላሽ እንደማይሰጧቸው ለማረጋገጥ ተችሏል።

በመሆኑም የጥናቱ ውጤት የሚያሳየን መምህራን የጽህፈት ትምህርት በተግባር እንደማያስተምሯቸው ወይም ቢያስተምሯቸውም ለሰጡት መለመጃ ተገቢውን ማስተካከያ እንደማይሰጡ ነው፡፡ ይህም ደግሞ የጽህፈት ትምህርት ክሂል ስለሆነ ተማሪዎቹ በተግባር እንዲማሩት ካላደረግንና ለስህተታቸው ተገቢውን ማስተካከያ ካልተሰጣቸው የጽህፈት ክሂልን ሊያዳብሩ አይችሉም። ቀጥለን ደግሞ ይህንኑ መረጃ የሚያጠናክርልንን የተጠኝ ተማሪዎችን ምላሽ እንመሌከት።

ሰንጠረዥ14. ተጠኝ ተማሪዎች የጽህፈት ትምህርት ስማር ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥልኝ መምህሩ ነው ለሚለው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ የሚያሳይ ሰንጠረዥ

| ጥያቄ | አማራጭ መልሶች | የመላሾች ብዛት | በመቶኛ/በ ፐርሰንት | የመላሾች ብዛት | መቶኛ /በፐርሰንት |
|---|---|---|---|---|---|
| | | አማርኛ አፍ ፈት | አማርኛ አፍ ፈት | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት | አማርኛ ኢ-አፍ ፈት |
| የጽህፈት ትምህርት ስማር ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥለኝ መምህሩ ነው | ፈጽሞ አልስማማም | 5 | 33.33% | 4 | 18.18% |
| | አልስማማም | 5 | 33.33% | 12 | 54.54% |
| | እስማማለሁ | 5 | 33.33% | 6 | 27.27% |
| | በጣም እስማማለሁ | 5 | 0% | 0 | 0% |

ከላይ በቀረበው የጥናት ውጤት ለመረዳት እንደሚቻለው ከአማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ውስጥ 66.66% የሚሆኑት ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥልኝ መምህሩ ነው ለሚለው የጽሐፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ መምህሩ እንደሚመርጥላቸው የገለጹ ሲሆን 33.33% የሚሆኑት አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ደግሞ ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥልኝ መምህሩ ነው ለሚለው የጽሐፍ መጠይቅ የሰጡትን ምላሽ መምህሩ እንደማይመርጥላቸው የሰጡት መረጃ ያመለክታል።

በሌላ በኩል ከአማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ውስጥ 72.72% የሚሆኑት ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥለኝ መምህሩ ነው ለሚለው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ መምህሩ እንደሚመርጥላቸው የተገኘው መረጃ ሲያመለክት 27% የሚሆኑት ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥልኝ መምህሩ ነው ለሚለው የጽሁፍ መጠይቅ የሰጡት ምላሽ መምህሩ እንደማይመርጥላቸው የተገኘው መረጃ ያሳያል። ከዚህ የጥናት ውጤት መረዳት እንደሚቻለው አማርኛ አፍ ፈትም ሆኑ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች አብዛኞቹ በጽህፈት ትምህርት ጊዜ የድርሰት ርዕስ በራሳቸው እንደማይመርጡ እና በመምህራን አስገዳጅነት ርዕስ እንደሚሰጣቸው ጥናቱ ያመለክተናል።

በመሆኑም የጽህፈት ክሂልን ይበልጥ ለማዳበር ተማሪዎች በራሳቸው ፍላጎት ርዕስ ቢመርጡ የሚያውቁትን ነገር መነሻ ስለሚያደርጉ ድርሰቱን ለመፃፍ የሀሳብና የቃላት ችግር አይገጥማቸውም፡፡ ምክንያቱም ከሚያውቁት ነገርና ከፍላጎታቸው የመነጨ ስለሚሆን ብዙ አይቸገሩም። ነገር ግን በመምህሩ የሚመረጥላቸው ከሆነ ያለፍላጎታቸው ስለሚጽፉ የሀሳብና የቃላት ችግር ሊገጥማቸው ይችላል። ከዚህም በላይ የጽህፈት ትምህርትን እንዲጠሉ ያደርጋቸዋል፡፡ በመሆኑም መምህሩ በጽህፈት ትምህርት ወቅት አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች ርዕስ መርጠው እንዲጽፉ ቢያደርግ የተሻለ ነው፡፡ ነገር ግን የድርሰት ርዕስ በተማሪዎች ይወሰን ማለት ሳይሆን ክሂልን እያዳበሩ ሲመጡ በመምህሩ በሚሰጣቸው ርዕስ ለመፃፍ ብዙም አይቸገሩም።

# ምዕራፍ አምስት
# 5. ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1 ማጠቃለያ

የዚህ ጥናት ዓላማ በዶዮና ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት አማርኛ አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት ማድረግ ነው፡፡ ስለዚህ በምዕራፍ አንድ በጥናቱ ዓቢይ አላማ ስር ለተነሱት አምስት ንዑስ አላማዎች እና በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ላይ ለተጠቀሱት ሁለት መሠረታዊ የምርምር ጥያቄዎች መልስ መስጠት ነው።

በመሆኑም የምርምሩ ንዑስ አላማዎች ድርሰት ሲጽፉ የቃላት ምርጫና አጠቃቀማቸውን መመርመር፤ በቋንቋው ህጎች /ስዋሰው/ የመጠቀም ችሎታቸው ምን ላይ እንደሚገኝ መገምገም፤ የስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ መፈተሽ፤ እንዲሁም በአጠቃላይ በጽሁፍ ክሂል ላይ ያላቸውን ፍላጎትና ልምድ ማጥናት እንዲሁም ከአማርኛ አፍ ፈትና ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችግር በየትኞቹ ተማሪዎች ላይ ይሰተዋላል? በጽህፈት ችሎታቸውስ የትኞቹ ይሻላሉ? ለሚሉት በጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ላይ ለተጠቀሱት ሁለት መሠረታዊ የምርምር ጥያቄዎችን ለመመለስ በተካሄደው ጥናት የሚከተለውን የጥናት ውጤት አስገኝቷል።

የቃላት አጠቃቀምን በተመለከተ አማርኛ ቋንቋ አፍ ፈት ተማሪዎች የተመዘገበባቸው ስህተት መጠን አማርኛ ቋንቋ ኢ-አፈ ፈት ከሆኑት ተማሪዎች ያነሰ ስለሆነ የተሻለ የቃላት አጠቃቀም ችሎታ እንዳላቸው በጥናቱ ለማወቅ ተችሏል።

በተጨማሪም ከጥናት ውጤቱ መረዳት እንደተቻለ አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ከኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች አማርኛ ቋንቋ አፍ ፈት ተማሪዎች የተመዘገበባቸው ስህተት መጠን አማርኛ ቋንቋ ኢ-አፍ ፈት ከሆኑት ተማሪዎች ያነሰ እንደሆነ በጥናቱ ያስመዘገቡት ውጤት ያመለክታል። በሌላ በኩል ደግሞ አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በቃላት አጠቃቀምና በአረፍተ-ነገር አወቃቀር በጣም ችግር እንዳለባቸው የተደረገው ጥናት ውጤት ያመለክታል። ነገር ግን በስርዓተ-ነጥቦች አጠቃቀምን በተመለከተ ከጥናት ውጤቶች መገንዘብ እንደተቻለው በጠቅላላ ድምር ውጤት አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ከአፍ ፈት ተማሪዎች በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ችሎታቸው የተሻሉ እንደሆነ ያመላክታል። በመሆኑም በዚህ የተገኘው ውጤት ይበል የሚያስብል

ቢሆንም አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ላይም ከፍተኛ ትኩረት ሰጥቶ መስራትን ይጠይቃል።

በአንቀጽ አደረጃጀትና አጠቃቀም በተደረገው የጥናት ውጤት መገንዘብ እንደተቻለው አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ከኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በአንቀጽ አደረጃጀት ችሎታቸው የተሻሉ እንደሆነ ያስመዝገቡት የስህተት መጠን ያመለክታል።

በመጨረሻም በተማሪዎች የድርሰት ጽህፈት ፍላጎትና መምህራን ለጽህፈት ትምህርት በሚሰጡት ትኩረት ላይ በተደረገው ጥናት ተማሪዎች ድርሰት ለመፃፍ ከፍተኛ የሆነ ተነሳሽነት እንዳላቸው ከተደረገው ጥናት ውጤት ማወቅ ተችሏል። ነገር ግን ፍላጎት ብቻውን ስኬት አይሆንም፡፡ የጽህፈት ትምህርት በተግባር የተደገፈ፣ ተከታታይ የሆነ እና ተግባርነቱ የበዛ እንዲሁም የመምህራንን ክትትልና ምግበ ምላሽ የሚጠይቅ ነው። ሆኖም ከጥናቱ የተገኘው ውጤት መምህራን ለክሂል ትኩረት ሰጥተው እንደማያስተምሩ እና ቢያስተምሩም ተማሪዎች ለሚጽፉት ድርሰት በራሳቸው ፍላጎት የሚመርጡት ርዕስ ሳይሆን በመምህራኑ እደሚመረጥላቸው ጥናቱ ይጠቁማል። በተጨማሪም ተማሪዎች ለፃፉት ድርሰት መምህራኑ ወዲያውኑ ምግበ ምላሽ እንደማይሰጧቸውና ስህተታቸውን አውቀው ለወደፊት የተሻሉ ሆነው ለመገኘት የሚያስችላቸው ሁኔታ እንዳሌላቸው በጥናቱ ተረጋግጧል።

## 5.2 አስተያየት

የጽህፈት ትምህርት ከፍተኛ ትኩረትን ከሚጠይቁ የቋንቋ ክሂሎች አንዱ ነው፡፡ በመሆኑም ተማሪዎች ይህን ክሂል በአግባቡ እንዲያዳብሩትና ተገቢውን እውቀት እንዲጨብጡ በመማር ማስተማሩ የሚደረገው የመምህራን ድጋፍና ክትትል በማያቋርጥ ሁኔታ መተግበር ቢችሉ የተሻለ ነው።

በመሆኑም አማርኛ አፍ ፈትም ሆነ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የመፃፍ ክሂልን በከፍተኛ ደረጃ የትምህርት እርከን ላይ የሚያዳብሩት ሳይሆን ከታች ከዝቅተኛ ደረጃ ወይም ከመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ጀምሮ መምህራን ለዚህ ትምህርት ትኩረት ሰጥተው፣ በእቅድና በተደራጀ መልኩ የፊደላትን ስርዓት፣ የስርዓተ ነጥቦችን አጠቃቀም፣ የቃላት አመራረጥና አጠቃቀም የመሳሰሉትን ለተማሪዎቻቸው ማስተማር ሲችሉ ነው። ከዚህም በተጨማሪ በመማር ማስተማሩ ሂድት መምህሩ የተማሪዎችን የጽሕፈት ክሂል ለማዳበር በምን አይነት መንገድ ትምህርቱ ቢከናወን ውጤታማ ይሆናል? የሚለው ጉዳይ ላይ ትኩረት ቢሰጡበት የተሻለ ይሆናል። ተማሪዎቹ ምን አይነት ተግባራትን

ቢያከናውኑ የመፃፍ ክሂላቸውን ያዳብራሉ? የሚሉት ጉዳዮች ላይ በደንብ መስራቱ ተገቢ ነው። እንዲሁም ተማሪዎቹ በጽህፈት ክሂላቸው ለሚፈጽሙት ስህተት እንዴት መረዳት እንዳለባቸውና ስህተታቸውን እንዴት ማስተካከል እንደሚገባቸው መምህራን ድጋፍ ቢያደርጉ የተሻለ ይሆናል።

ስለሆነም በዚህ ጥናት የተገኘው ውጤት የሚያሳየን ተማሪዎቹ በተለያዩ የጽህፈት ክሂል የተለያዩ ደረጃ ላይ እንዳሉ ነው። ለምሳሌ በቃላት አጠቃቀምና ሰዋስው አማርኛ አፍ ፈት ተማሪዎች ከኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የተሻሉ ሲሆኑ በስርዓተ-ነጥብ አጠቃቀም ደግሞ አማርኛ ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ከአፍ ፈት ተማሪዎች የተሻሉ መሆናቸውን ጥናቱ አመለክቷል። እንዲሁም ሁለቱም ቡድኖች ያላቸውን የክሂል ክፍተት እንዲያጠቡ የመምህሩ ሚና ከፍተኛ በመሆኑ ለተማሪዎቹ ድጋፍና ክትትል ቢያደርግ የተሻለ ይሆናል። ይሄውም መምህሩ ተማሪዎች የግልና የቡድን ስራ እንዲሰሩ በማድረግ አንዱ ተማሪ ከሌላው እየተማረ የክሂል እውቀት ክፍተታቸውን የሚሞሉበትን መንገድ ማመቻቸት አንድና ተመራጭ መንገድ ነው። ሌላው ደግሞ መምህራን በጽህፈት ትምህርት ጊዜ በተማሪዎች ላይ ጫና ሳይፈጥሩ ተማሪዎቹ በፍለጉት ርዕስ ላይ ድርሰት እንዲጽፉ በማድረግና ድርሰቶችን አይተው ችግራቸውን እንዲቀርፉ ግብረ-መልስ መስጠት ይኖርባቸዋል። ነገር ግን ይህን ክፍተት መምህራኑ እያጠበቡና እየቀረፉ ካልሄዱ የተማሪዎቹ የጽህፈት ክሂል ክፍተት አብሯቸው ይጓዝና ትውልድ አማርኛ የመማር ፍላጎታቸው እንዳይጠፋ አስፈላጊ ጥንቃቄ መደረግ አለበት።

## ዋቢ ጽሁፎች

ልዑልሰገድ አሰፋ። (1997)። በወላይታና ሲዳመኛ ተናጋሪዎች በአማርኛ ድርሰት ውሰጥ የታዩ ስህተቶችና የስህተት ምንጮች ትንተና። ለሁለተኛ ዲግር ሟሟያ የቀረበ ጥናት፣አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)

ምህረት ሳዳሞ። (1998)። በዋቻሞ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በሀድይኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና። ለሁለተኛ ዲግር ማሟያ የቀረበ ጥናት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)

ሰይድ ይመር። (1993) ። "በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የቀረቡትን የጽህፈት ትምህርት ሥነጽሐፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ-ምረቃ መረሀ-ግብር፣ (ያልታተመ)። (ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)። (ያልታተመ)

በድሉ ዋቅጅራ። (2007)። በስነጽሐፍ ቋንቋን ማስተማር። (ሁለተኛ እትም)፣ አዲስ አበባ፣ ንግድ ድርጅት

ባየ ይማም። (2000)። የአማርኛ ሰዋስው። የተሻሻለ ሁለተኛ እትም፣ አዲስ አበባ፣ እሌኒ ማ.ኃ.የተ. ቤት ናሙናነት"። አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ተንተና።

ተገኝ አህመድ። (2000)። አፋቸውን በከፍኛ ቋንቋ የፈቱ የቦንጋ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ሰልጣኝ መምህራን በአማርኛ ቋንቋ ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች ትንተና። ለሁለተኛ ዲግር ማሟያ የቀረበ ጥናት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ። (ያልታተመ)

ትምህርት ሚኒስቴር (1970) ለሁለተኛ ደረጃ የአማርኛ ስርዓተ ትምህርት ከ7-12ኛ ክፍል። አዲስ አበባ። ከስርዓተ ትምህርት ሱፐር ቪዥንን መመሪያ በአማርኛ ትምህርት ቡድን የተዘጋጀ። (ያልታተመ) ትምህርት ቤቶች ውስጥ 11ኛ ክፍል

ተማሪዎች የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት"። ንግድ ማተሚያ ድርጅት።

አማረ ማሞ፡፡ (1986)፡፡ የልብወለድ ድርሰት አፃፃፍ መሠረታዊ መመሪያ።
አዲስ አበባ፣

አቢይ አሰፋ። (1997)። አዲስ ከተማ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
እና በደብረ ኃይል ቅዱስ ራጉኤል ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት
የዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ሲጽፉ የሚፈጽሟቸው ስህተቶች
ተንተና። (ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)። (ያልታተመ)

አለማየሁ ተመስገን። (1998። "አዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር በሚገኙ ሁለት
የመንግስትና የግል ትምህርት ቤቶች ውስጥ 11ኛ ክፍል ተማሪዎች
የጽህፈት ክሂል ችሎታ ንጽጽራዊ ጥናት"። አዲስ አበባ፣ ዩኒቨርሲቲ
(ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት)። (ያልታተመ)

ኢሳያስ ይልማ፡፡ (2002)። "የጽሐፍ ክሂልን በመማር ማስተማር ሂደት ውስጥ
የትምህርት አደረጃጀታቸው ክፍል። አዲስ አበባ። (ለሁለተኛ ዲግሪ
ማሟያ የቀረበ ጥናት)። (ያልታተመ)

ያለዉ እንዳወቅ። (2001)። የምርምር መሠረታዊ መርሆዎችና አተገባበር።
(ሁለተኛ እትም)፣ ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነዘዴ ትግበራ"።
አዲስ አበባ፣ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ደብሬ ተሰማ (1990) በኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ የአስራ አንደኛ ክፍል ተማሪዎች
ድህረ-ምረቃ መርሃ-ግብር፣ (ያልታተመ)። ፎክሎር ትምህርት ክፍል ድህረ-
ምረቃ መረሀ-ግብር፣ (ያልታተመ)።

Abiy Y. (2013). High School Students' Writing Skills and their English Language Proficiency Acquisition Research and its Implication. Cambridge: Cambridgeacross L1s, genres, and language ratings. Journal of Second Language Writing 32

Allwright.Dand K.M Bailey(1991) Focus on the Language class room Research Approaches. (3rd Ed), University of Nebraska-Lincoln.as Predictors of their English Language Writing Performance. Bahir Dar Publishers Ltd. Boston: Heinle and Heile Publishers.

Broughtonm, G and Etal (1978) Teaching English As a Foreign Language. London, R udedge.

Brown, H, (1994) Principles of Language Learning and Teaching. New Jersey:

Byrne, D. (1991). Teaching Writing Skills. London: Longman Group, UK Cambridge University Press

Course in Applied Lingustics. Vol.3 (PP.

Creswell, J. W. (2009). Research Design, Qualitative, Quantitative, & Mixed Method

Davies, A. and Widdowson. H. G. (1974). "Reading and Writing". In J.P.B. Allen & S.Pit

Day,S.(1984) The Writers Work Book New York: Macgraw Hill Company.

For Language Teachers Cambridge Cambridge university press for Language Teaching. (2nd Edition), Cambridge University Press. Group, UK limited. Group, UK limited.

Harmer, J. C. (1991). The Practice of English Language Teaching. London: Longman

Heaton, J,B.(1998) Writing English Language Tests. New York: Longmaninc.

Heaton, J. B. (1990). Writing English Language Tests. (3rd Edition), London: Longman

Hedge, T. (1988). Writing. Oxford: Oxford University Press. Hughes, A. (2003). Testing

Kamrul, Md. H. and Mohd. M. A. (2010). Approaches to Writing in EFL/ESL Context:

Kroll, B. (1990). „„,What Does Time Buy ? ESL Student Performance on Home Versus Language Teaching Journal, 25,204-219limited.

Celece-Murcia, M. (2001). Teaching English as Second or Foreign Language. (3rd ed.),

Littlewood, W.(1986) Foreign and Second Language Learning Language London and New Yoyk: Longman Group Ltd.

Norish, J.(1992) Language Learners and their Errors. London: Macmillan

Norrish, H.J.(1983) Language Learners and their Reeor: London and

Norrish, J. (1990). Language Learners and their Errors. London: Macmillan Publishers Ltd.

Nunan, D. (1989). Designing Tasks for the Communicative Classroom. Cambridge:

of Current Practice. Cambridge: Cambridge University Press. Staples, S. and Randi,

Pincas, A. (1982). Teaching English Writing. London: Macmillan Publishers Ltd. Prentice Hall. Publishers Ltd.

R. (2016). Understanding First-year L2 Writing: A lexico-grammatical analysis

Raimes, A. (1983). Techniques in Teaching Writing. Oxford: Oxford University Press.

Richards, J and Renandya, A. (2002). Methodology in Language Teaching An Anthology

Richards, J. C. (1990). The Language Teaching Matrix. Cambridge: Cambridge University Press.

Richards, J.C.(1974) Error Analysis perspectives on second Language Analysis.

Richards,J.c.(1971) ‹‹ A non-contrastive approach to Error Analysis> English Sc. Vol. 9 No. 1 September 2013.

Trimmer, J. and James, M. (1988). Writing with Purpose. Boston: Houghton Mifflin Company. UK limited. University press University, Faculty of Humanities, Department of English, Ethiop. J. Educ. &

Ur, P. (1996). A Cource in Language Teaching. Cambridge: Cambridge University Press. Vol. 15 No. 1-2 December 2010 Kenworthy, R. (2006). TESL/EJ Teaching English as a Second or Foreign Language. (Volume 10 Number 1), Ohio University, Hong Kong.

Zamel, V. (1985). “Responding to Student Writing” TESOL Quarterly. 191, (PP.79-101).

# አባሪ "ሀ"
# በጅማ ዩኒቨርሲቲ

## ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

**ለድህረ-ምረቃ ምርምር በተማሪዎች የሚሞላ የምርምር ጥያቄዎች**

በዶዮ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

## ክፍል አንድ

**ውድ ተማሪዎች ;-**

የዚህ መጠይቅ ዓላማ፡- በዶዮ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል አማርኛ ትምህርት ተማሪዎች አፍ ፈትና ኢ-አፍፈት ተማሪዎች ላይ በማተኮር በጽህፈት ክሂል ችሎታ የትኞቹ ተሽለው እንደሚገኙ በማነፃፀር ለመለየት የሚያስችል መረጃ ለማሰባሰብ፣ ችግሩን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብና ተማሪዎቹ ወደ አስራ አንደኛ ክፍል ሲደርሱ በራሳቸው ላይ የሚታየውን ችግር በመቅረፍ የጽህፈት ችግር መቅረፍ የሚያስችላቸውን መንገድ መጠቆም ነው፡፡

ስለዚህ መጠይቁን በጥንቃቄ አንብባችሁ ተገቢውን መልስ በመሙላት ቀና ትብብራችሁን እንድታደርጉ ትጠየቃላችሁ፡፡ በመሆኑም ውድ የሆነውን የትምህርት ጊዜያችሁን መስዋዕት በማድረግ ምታድርጉልኝ ቀና ትብብር ሁሉ በቅድሚያ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡-

1. በመጠይቁ ላይ ስም አይፃፍም

2. መጠይቁን ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው፡፡

ክፍል ሁለት  አጠቃላይ መረጃ

II, ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በማንበብ ክፍት ቦታዎችን ሙሉ፤፤

1. ፆታ;- ________ 2. የአፍ መፍቻ ቋንቋ;- ______________________

ክፍል ሶስት

III, ከዚህ በታች በሰንጠረዥ የቀረቡት ጥያቄዎች አራት አማራጮችን ይዘዋል፡፡ ከቀረቡት አማራጮች ውስጥ ለቀረቡት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ነው የምትሉትን በመምረጥ በሳጥኑ ውስጥ "X" ምልክት በማድረግ አመልክቱ፡፡

1. ፈጽሞ አልስማማም 2. እስማማለሁ 3. አልስማማም 4. በጣም እስማማለሁ

| ተቁ | ጥያቄዎች | 1 | 2 | 3 | 4 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | የትምህርት ክፍል መምህራን በጽህፈት ወቅት ስለምጠቀምባቸው የተለያዩ የቃላት ምርጫ አስተምረውኛል | | | | |
| 2 | ድርሰትን ስጽፍ ሰዋስውን በአግባቡ እጠቀማለሁ | | | | |
| 3 | የትምህርት ክፍል መምህራን ስለአማርኛ ስርዓ-ተነጥቦችና አጠቃቀም አስተምረውኛል | | | | |
| 4 | ድርሰት ስጽፍ የአንቀጽ አንድነት፣ ተክክለኛነትንና ጉልህነትን ጠብቄ እጽፋለሁ | | | | |
| 5 | የምጽፈው ድርሰት ትክክለኛ የፊደል አጣጣል ይዞ የሚጓዝ ስለሆነ አንባቢዎቼ ሳይቸገሩ ያነቡታል | | | | |
| 6 | የአማርኛ ድርሰት ለመፃፍ ፍላጎት አለኝ | | | | |
| 7 | የትምህርት ክፍል መምህራን በክፍል ውስጥም ይሁን ከክፍል ውጪ የሚሰጡትን የጽህፈት መልመጃዎች አርመው ማስተካካያ ይሰጣሉ | | | | |
| 8 | የጽህፈት ትምህርት ስማር ድርሰት ለመጻፍ ብዙ ጊዜ ርዕስ የሚመርጥልኝ መምህሩ ነው | | | | |
| 9 | ድርሰትን ስጽፍ ትክክለኛ የቃላት አጠቃቀምና ስርዓተ-ነጥቦችን በአግባቡ እጠቀማለሁ | | | | |

# አባሪ "ለ"
# በጅማ ዩኒቨርሲቲ

### ድህረ-ምረቃ ትምህርት ቤት

ለድህረ-ምረቃ ምርምር በተማሪዎች የሚሞላ የምርምር ጥያቄዎች

በዶዮ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል ተማሪዎች የሚሞላ የጽሑፍ መጠይቅ

ክፍል አንድ

ውድ ተማሪዎች፡-

የዚህ መጠይቅ ዓላማ፡- በዶዮ 2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ10ኛ ክፍል አማርኛ ትምህርት ተማሪዎች አፍ ፈትና ኢ-አፍፈት ተማሪዎች ላይ በማተኮር በጽህፈት ክሂል ችሎታ የትኞቹ ተሸለው እንደሚገኙ በማነፃፀር ለመለየት የሚያስችል መረጃ ለማሰባሰብ፤ ችግሩን በመለየት የመፍትሄ ሀሳብ ማቅረብና ተማሪዎቹ ወደ አስራ አንደኛ ክፍል ሲደርሱ በራሳቸው ላይ የሚታየውን ችግር በመቅረፍ የጽህፈት ችግር መቅረፍ የሚያስችላቸውን መንገድ መጠቆም ነው፡፡

በዚህ መሠረት ከዚህ በታች የቀረቡት የድርሰት ርዕሶች በየጊዜው ከሚሰጡት የክፍል ውስጥ ፈተናዎች ወይም በመንፈቅ-ዓመቱ መጨረሻ ከሚሰጡት የማጠቃለያ ፈተናዎች ጋር ግንኙነት የሌላቸው ስለሆነ ውጤቱ አይያያዝም ወይም ከተፈተናችሁትም ሆነ ወደ ፊት ከምትፈተኑት ፈተናዎች ውጤት ጋር አብሮ አይደመርም፡፡ ስለዚህ ምንም አይነት ስጋት ሳይኖራችሁ በነፃነትና ትኩረት በመስጠት በትዕዛዙ መሠረት ከዚህ በታች ለቀረቡት የድርሰት ርዕሶች በምትጽፉት ድርሰት ለምታደርጉልኝ ቀና ትብብር ሁሉ በቅድሚያ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባሀሁ፡፡

ማሳሰቢያ፡-

1. በመጠይቁ ላይ ስም አይፃፍም

2 መጠይቁን ከጓደኛ ጋር ተመካክሮ መሙላት የጥናቱን ውጤት ስለሚያዛባ የተከለከለ ነው፡፡

ክፍል ሁለት

አጠቃላይ መረጃ

II, ከዚህ ቀጥል የቀረቡትን ጥያቄዎች በማንበብ ክፍት ቦታዎችን ሙለ

1. ፆታ;- ________

2. የአፍ መፍቻ ቋንቋ;- ____________________________

ክፍል ሁለት

III, ከዚህ ቀጥሎ አስር የድርሰት ርዕሶች ቀርበዋል፤ ከአስሩ ውስጥ ይበልጥ ሀሳባችሁን ልትገልጹበት የሚያስችላችሁን ርዕስ በመምረጥ 150-350 በሚደርሱ ቃላት ድርሰት ፃፉ፡፡

1. የጊቤ ወንዝ ጥቅም

2. ዘመናዊ እርሻ በጅማ ዞን

3. የበረሃ አስቸጋሪነት

4. የወባ በሽታ መተላለፊያ መንገዶች

5. የአቮካዶ ጥቅም

6. የፊሾ እርሻ ምርምር

7. የዛፍ ጥቅም

8. የሀገር ፍቅር

9. የጓደኛ ታማኝነት

10. የጎበዝ ተማሪ ተግባር

# አባሪ “ሐ”

## የድርሰት እርማት መስፈርት

ውድ መምህራን

ከዚህ በታች የተሰጠውን የእርማት መስፈርት ትርጉም በመጠቀም በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚታዩትን ስህተቶች ለይታችሁ በማውጣት የስህተቶቹን አይነትና ብዛት በተዘጋጀው ቅጽ ላይ አስፍሩ፡፡ በመሆኑም ውድ ባልደረቦቼ የተጣበበ ጊዜያችሁን መስዋዕት በማድረግ ለምታደርጉልኝ ቀና ትብብር ሁሉ በቅድሚያ የከበረ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡

የማረሚያ መስፈርት ትርጉም

1. የቃላት አጠቃቀም ስህተት

    1.1 የቃላት ድግግሞሽ

    1.2 የቃላት ድረታ

    1.3 ባዕድ ቃላት

2. ሰዋስዋዊ አጠቃቀም ስህተት

    2.1 የቁጥር ስህተት

    2.2 የመደብ አጠቃቀም ስህተት

    2.3 የቃላት ቅደም ተከተል ስህተት

    2.4 የቅጥያ አጠቃቀም ስህተት

3. የአንቀጽ አወቃቀር ስህተት

    3.1 የአንቀጽ ጉልህነት አለመኖር

    3.2 የአንቀጽ መሸጋገሪያ አጠቃቀም ስህተት

    3.3 የአንቀጽ አንድነት

    3.4 የአንቀጽ ተያያዥነት

4. ስርዓተ-ነጥቦችን በአግባቡ አለመጠቀም

4.1 አራት ነጥብ

4.2 ነጠላ ሰረዝ

4.3 ትምህርተ ጥቅስ

4.4 የጥያቄ ምልክት

5. ትክክለኛ የድርሰት ቅርጽና የፊደላት ቅርጽ አለመጠቀም

5.1 ትክክል ያልሆኑ የፊደላት ቅርጽ አጠቃቀም

5.2 የህዳግ አጠቃቀም ስህተት

5.3 ፊደል ግድፈትና ጭመራ

5.4 ስርዝ ድልዝ